የአብክመ ገቢዎች ቢሮ
ANRS Bureau of Revenue
ስለምናገለግልዎ ደስታ ይሰማናል - Serve with Passion

ቁጥር ገቢዎች 4.1/369
Ref.No
ቀን 25/10/2018

ለ14ቱ ዞን አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ
ለ8ቱ ሪጅአፖሊታን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ
በያሉበት

ጉዳዩ፡-የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅን ስለመላክ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ምክር ቤት 6ኛ ዙር ፣ 4ኛ ዓመት ሥራ ዘመን፣ 10ኛ መደበኛ ጉባኤ የክልላችን የገቢ ግብር አዋጅ ለማሻሻል ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ መስተዳድር ምክር ቤቱ አዋጁን መርምሮ እንዲያጸድቅ በተሰጠው ውክልና መሰረት የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 301/2018 ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም የገቢ ግብር አዋጁ ወደ እንግሊዘኛ ተቀይሮ አስከሚታተም የተሻሻለውን የገቢ ግብር አዋጅ 82 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን የአዋጁ ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንድታደርጉ በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡

"ግብር ለሀገር ክብር "

መንገሻ ፈንታው ንጋቱ (ዶ/ር)
Mengesha Fentaw Nigatu (PhD)
ቢሮ ኃላፊ
Bureau Head

ግልባጭ

- ለደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት
- ለግብር አወ/አሰ/ክት/ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ ኦዲትና ህግ ማስከበር ዋና ሥራ ሂደት
- ለግብር ትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ ኢንተሊጀንስ ዋና የሥራ ሂደት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት
- ለታክስ ጉዳዮች አማካሪ

ገቢዎች ቢሮ

ባህር ዳር

TA/EG

D:Gen.Dir./Letters&memos/Letter2

☎ 058 226 57 76 /058 226 57 74
Fax 058 222 20 71 /058 226 57 80
Email- amhararevenue@ethionet.et
✉ 746

አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፩/፪ሺ፬፲፰ ዓ.ም.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ

በገቢ ግብር ስርአት ላይ ለውጥ በማድረግ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል የሚያርፍበትን የግብር ጫና መቀነስ፣ የመንግስትን ገቢ አሰባሰብ ማሻሻል እና ለኢኮኖሚው እድገት የሚያግዝ ዘመናዊ፣ ተላልና ቀልጣፋ የግብር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የታክስ ማስከፈያ ምጣኔው ከወቅታዊው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችል ማስተካከያ ለማድረግ፣ የታክስ መሰረቱን ለማስፋት እና ውጤታማ የሆነ የታክስ ማበረታቻ ስርዓት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ፣

በየሰበት ወሩ የግብር አከፋፈል ሥርዓት በመዘርጋት የአነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች የግብር አከፋፈል ስርአት ቀላል እንዲሆን ማድረግ፣ በአመቱ መጨረሻ በግብር ክፍያ ላይ የሚከሰተውን ጫና መቀነስ እና መንግስት በወቅቱ ገንዘቡን ሰብስቦ ለፕሮጀክቶች ማሰረጃሚያ እንዲያውል ማድረግ፣

ካፒታልን በማቀናጀት ለኢንቨስትመንት ተግባር ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እና ግልጽነት ሰፍኖባቸው አንቀጾች ምክንያት የሚፈጠረውን ውጣ ውረድን ማስቀረት፣

ለታክስ ማጭበርበር ምቹ ሁኔታን ከፈጠሩ አፈጻጸሞች አንዱ በጥሬ ገንዘብ የሚፈጸም ክፍያ በመሆኑ፣ በዚህ እና በሌሎች መንገዶች ከታክስ ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ሳመቀላክል በሚያስችል መልኩ የገቢ ግብር አዋጁን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፶፱ ንዑስ አንቀፅ ፫(፩) ቤተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፩/፪ሺ፬፲፰ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፱. <u>ትርጉም</u>

በክልሉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ አዋጅ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ አዋጅ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

፩). "**የገንዘብ መጠን**" በዓይነት የተገለፀ መጠንንም ይጨምራል፡፡

፪). "**የንግድ ሥራ**" ማለት፣

ሀ/ በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛውም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም ቮኬሽናል ሥራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣

ለ/ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ነው ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ ማንኛውም ሥራ፣ ወይም

ሐ/ ሕንጻ ማከራየትን ሳይጨምር የኩባንያው ዓላማ ምንም ቢሆን ማንኛውም የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚሠራው ማንኛውም ሥራ፡፡

፫). "**የንግድ ሥራ ሀብት**" ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ የንግድ ሥራ ሀብት ነው፡፡

፬). "**የንግድ ሥራ ገቢ**" ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ ፣ የንግድ ፣ የግብርና ፣የሙያ ወይም የጣልቃ ገብ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ፣በኢትዮጵያ የንግድ ህግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና ከተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ ሲሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፩ የተሰጠውን ትርጉም ይጨምራል፡፡

፭). " **ማግኘት**" ማለት፣

ሀ/ ለንግድ ሥራ እና ለኪራይ ገቢ ግብር፤

፩. በተሰብሳቢና ተከፋይ የሒሣብ አያያዝ ዘዴ ሒሳቡን ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፣

፪. ሒሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ለሚይዝ ግብር ከፋይ፣ መቀበል፣ ወይም

ለ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተጣለ ማንኛውም ሌላ ግብር፣ መቀበል ነው፡፡



፮). **"የትርፍ ድርሻ"** ማለት አንድ ድርጅት ለአባላቱ የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ/ የድርጅቱ ካፒታል በከፊል ሲቀንስ ለአባሉ በአባልነቱ ተመላሽ የሚደረግለት ከካፒታሉ ውስጥ ከተቀነሰው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፣

ለ/ ድርጅቱ መልሶ በመሸጡ ወይም በመዘጋቱ ወይም ኩባንያው በመፍረሱ ወይም ሽርክና በመቋረጡ ምክንያት የአባልነት ጥቅም ሲሰረዝ ለአባሉ ተመላሽ የተደረገለት በካፒታሉ ውስጥ ከነበረው በስሙ ከተመዘገበ የአባልነት ጥቅም ዋጋ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን፣

ሐ/ ድርጅቱ ለአንድ የድርጅት አባል ወይም ከአባሉ ጋር ግንኙት ላለው ሰው ትርፍ የማከፋፈል ውጤት በሚያስከትል ግብይት ያበደረው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፣ ለአንድ ሀብት ወይም አገልግሎት የፈጸመው ክፍያ፣የቀረበ ማንኛውም ሀብት ወይም አገልግሎት ዋጋ፣ ወይም የተተወ የብድር ዕዳ፣

፯). **"ተቀጣሪ"** ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ሲሆን የድርጅት ዳይሬክተርን ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የሕዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ኃላፊን ያጠቃልላል፡፡

፰). **"ቀጣሪ"** ማለት ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው፡፡

፱). **"ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ"** ማለት ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተሰጠውን ትርጉም ይጨምራል፡፡

፲). **"ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ"** ማለት በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "ሠ" ከግብር ነፃ የሆነ ገቢ ነው፡፡

፲፩). **"የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች"** ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ የተደነገጉት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ናቸው፡፡

፲፪). "ጠቅላላ ገቢ" ማለት ወጪዎች ተቀናሽ ከመደረጋቸው በፊት አንድ ሰው ያገኘው በሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ሥር የሚወድቅ ጠቅላላ ገቢ ነው።

፲፫). "**የማይንቀሳቀስ ሀብት** " በአንቀጽ ፴፯ በተደነገገው መሠረት በማዕድን ወይም በነዳጅ ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን ወይም የነዳጅ መረጃን ይጨምራል።

፲፬). "**ገቢ**" ማለት መደበኛ ያልሆነ ገቢን ጨምሮ ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ወይም በማንኛውም መንገድ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው፣ በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ነው።

፲፭). "**ራሱን የቻለ ሥራ ተቋራጭ**" ማለት ሥራውን በአመዛኙ በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው።

፲፮). "**ወለድ**" ማለት ገንዘብን ለመጠቀም ወይም የክፍያ ጊዜን ለማራዘም በየጊዜው ወይም በአንድ ጊዜ የሚከፈል ገንዘብ ሲሆን ቀናሽን፣ ፕሪሚየምን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ክፍያዎችንም ይጨምራል።

፲፯). "**የሥራ አመራር ክፍያ**" ማለት ለሥራ አመራር ወይም አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ሲሆን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን አይጨምርም።

፲፰). "**ገቢዎች ቢሮ** "ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ነው።

፲፱). "**ቢሮ**" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብ ቢሮ ነው።

፳). "**መስተዳድር ምክር ቤት**" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ነው

፳፩). "**መቀበል**" የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ሀ/. ግብር ከፋዩ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በሕግ መሠረት ገንዘቡ በግብር ከፋዩ ስም ጥቅም ላይ ሲውል፣

ሰ/.ለግብር ከፋዩ ጥቅም ተብሎ ገንዘቡ መልሶ ሥራ ላይ ሲውል ወይም ሊጠራቀም ወይም ደግሞ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፣

ሐ/.ግብር ከፋዩ ጥቅም ወደ ባንክ ሂሳብ ውስጥ ሲገባ ወይም ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ ሲዘዋወር፣

መ/. በሌላ በማናቸውም መልኩ ለግብር ከፋዩ የተያዘለት ሲሆን፣

፳፱). "ሮያሊቲ" ማለት ከዚህ በታች ከተመለከቱት ለማንኛውም ጉዳይ በአንድ ጊዜ ወይም በየጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው።

ሀ/ ማንኛውንም የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ጥበብ፣ ወይም የሳይንሳዊ ሥራ የቅጂ መብት ሲሆን፣ የሲኒማቶግራፊ ፊልሞችና ለሬድዮ፣ለቴሌቪዥን ወይም ለኢንተርኔት ሥርጭት የሚውሉ ፊልሞችና፣ ቴፖችን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘትን ይጨምራል፣

ለ/ ከቴሌቪዥን ወይም ከሬድዮ ወይም ከኢንተርኔት ሥርጭት ጋር ተያይዞ በሳተላይት በኬብል፣በኦፕቲክ ፋይበር፣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ወይም የሚታዩ ምስሎችን፣ ወይም ድምፆችን ወይም ሁለቱንም መቀበል ወይም ለመቀበል የሚያስችል መብት ማግኘት፣

ሐ/ ማንኛውንም የፈጠራ ባለቤትነት መብት፣ ፈጠራ፣ የንግድ ምልክት፣ ንድፍ ወይም ሞዴል፣ ፕላን፣ የሚስጥር ቀመር ወይም ሂደት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ንብረት ወይም መብት መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፣

መ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣ የንግድ ወይም ሳይንሳዊ መሣሪያ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መብት ማግኘት፤

ሠ/ ማንኛውንም ኢንዱስትሪያዊ፣የንግድ ወይም ሳይንሳዊ ተሞክሮ የሚመለከት መረጃ መጠቀም ወይም የመጠቀም መብት ማግኘት፤

ረ/ በዚህ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ-ሠ) የተዘረዘሩትን ንብረቶች ወይም መብቶች መጠቀም እንዲቻል በተጨማሪነትና በተቀጽላነት የሚሰጥ ድጋፍ፤

ሰ/ የማእድን ፣ የኮንስትራክሽን፣ የደን እና የደን ውጤቶች ሮያሊቲ በክልሉ ሌሎች ህጎች የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡



፳፫). "**የግብር ዓመት**" ማለት

ሀ/ ለግለሰብ ሲሆን፣ ገቢዎች ቢሮ በጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ እና በጽሑፍ ማስታወቂያው የተወሰኑትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት ግለሰቡ የራሱን የሂሳብ ዓመት ካልተጠቀመ በስተቀር፣ ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ቀን ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው።

ለ/ ለድርጅት ሲሆን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት፣ ወይም

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ የተወሰነው የመሸጋገሪያ የሂሳብ ዓመት ነው።

፳፬). "**ግብር ከፋይ**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው

፳፭)."**የቴክኒክ ክፍያ**" ማለት ለቴክኒካዊ፣ ሙያዊ፣ ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን፣ የቴክኒክ ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለመጠቀም የሚከፈል ክፍያን ይጨምራል።

፳፮). "**የንግድ ዕቃ**" የሚከተሉትንም ይጨምራል።

ሀ/ ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፣

ለ/ በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ ዕቃ፣ ወይም

ሐ/ ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንስሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ

፳፯). "**ዋና ባለቤትነት**" ማለት በድርጅት ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ድርጅት ወይም ድርጅቶች ወይም በግለሰቦች አማካኝነት ወይም በግለሰብ ባለቤትነት ሥር ባለ ሆነ ተቋም አማካኝነት ይተዳደር የባለቤትነት ጥቅም ነው።

፳፰)."**ድርጅት**" ማለት ኩባንያ፣ የሽርክና ማህበር፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም ሌላ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ ሀገር የተመሠረተ የሰዎች ድርጅት ነው።

፳፱). **ኩባንያ**" ማለት የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ለመሥራት የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ ባሌላ ሀገር ሕግ መሠረት የተመሠረተን ተመሳሳይ የንግድ ድርጅት ይጨምራል።

ሻ). **"ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው"** ማለት ከሚከፍለው ክፍያ ላይ በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው::

ሸ፩). **"ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ"** ማለት በዚህ አዋጅ ክፍል አሥር መሠረት ግብር ተቀንሶ የሚያዝበት ገቢ ማለት ነው::

ሸ፪) **"ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ የተመለከቱት አነስተኛ ግብር ከፋዮች ለሚከፍሉት ግብር ስሌት መሰረት የሚሆን በአንድ አመት ውስጥ ከንግድ ስራቸው የሚያገኙት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው::

ሸ፫). **"ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ"** ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የቪዲዮ ማጋሪያ አገልግሎቶችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን፣ የድምጽ ማስተላለፊያ (ፖድካስት) አገልግሎቶችን እና የቀጥታ ስርጭት መድረኮችን ጨምሮ በአንላይን መድረኮች ላይ ዲጂታል ይዘትን በመፍጠር እና በማሰራጨት የሚያገኘው ማንኛውም የገንዘብ ወይም በዓይነት የሚገኝ ገቢ ነው:: ይህም የሚከተሉትን ገቢዎች ያካትታል፦

ሀ/ ማስታወቂያዎች እና ስፖንሰርሺፖች፣

ለ/ የምርት ስም ሰምምነቶች እና ድጋፎች፣

ሐ/ የአጋርነት ግብይት እና የምርት ምደባዎች፣

መ/ የደጋፊዎች አስተዋጽኦ፣ የገንዘብ ስጦታዎች ወይም የብዙሃን የገንዘብ ማሰባሰብ (ክራውድ ፈንዲንግ)፣

ሠ/ የአባልነት ክፍያዎች

ረ/ የዲጂታል ወይም የአካላዊ ሸቀጦች ሽያጭ፣

ሰ/ ለማስተዋወቂያ እንቅስቃሴ ምትክ የተገኙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና

ሸ/ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ክፍያዎች::

ሸ፬) **" የዲጂታል አገልግሎት"** ማለት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን የዲጂታል ይዘት ያለው አገልግሎት ነው::

፫. <u>የግብር ከፋይ ደረጃዎች</u>

፩. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፤

ሀ) የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፤

፩) ድርጅት፤ ወይም

፪) ጠቅላላ አመታዊ ገቢው ብር ፪ ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው፤

ለ) ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር አመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር ፪ ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) የሚያንስ ሰው ነው።"

፪. የገቢዎች ቢሮ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የግብር ማስታወቂያ ወይም የሚያገኘውን ሌላ ማናቸውም መረጃ መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን ይወስናል።

፫. ታክስ ከፋዩ የደረጃ ለውጥ ማድረግ የሚያስችል ሽያጭ በግብር ዓመቱ መፈጸሙን ከአረጋገጠ ከሚቀጥለው በጀት አመት ጀምሮ ለደረጃው የተቀመጡ ግዴታዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል።

፬. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተመለከተውን እና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ" ወይም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት አመት አንድ ጊዜ ማሻሻል አለበት።

፬. <u>በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት</u>

፭). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣(፫)፣(፬) እና (፭) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ "በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት" የሚባለው ማናቸውም ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው።

፪). ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ተደርገው ይወሰዳሉ።

ሀ/ ዋንኛ ተግባሩ የድርጅቱ አገናኝ ሆኖ ከሚያገልገል ጽ/ቤት በስተቀር የአስተዳደር ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፣ ቢሮ፣ ፋብሪካ፣ መጋዘን ወይም ወርክሾፕ፣

ለ/ የማዕድን ማምረቻ ሥፍራ፣ የግንባታ ጠጠር ማምረቻ፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የተፈጥሮ ሀብት ፍለጋ፣ ወይም ማምረት ሥራ የሚከናወንበት ቦታ፣

ሐ/ ማናቸውም ሰው ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሰራተኞችን በመመደብ የቴክኒክ አገልግሎት እና የምክር አገልግሎትን ጨምሮ የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት፤ አገልግሎቱ ወይም ተያያዥ የሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወነው የንግድ ስራ በአንድ የግብር አመት ወይም በማናቸውም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ድምር ከ፻፷ (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የተከናወነ ከሆነ፤

፫). የግንባታ ስራው የሚከናወንበት ቦታ፤ ፕሮጀክቱ ወይም የስራ እንቅስቃሴው በአንድ የግብር አመት ወይም በማናቸውም አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከ፻፷ (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የሚቆዩ እስከሆነ

ድረስ የህንጻ ግንባታው የሚከናወንበት ቦታ ወይም የኮንስትራክሽኑ ስራ፤ የመገጣጠሚያው ወይም የተከላው ፕሮጀክት ወይም ከነዚህ ጋር የተያያዙ የቁጥጥር ስራዎች በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት እንደሆነ ይቆጠራል።

፱). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል በመደበኛ የንግድ ሥራ አካሄድ ከሚያከናውነው ተግባር በስተቀር ማናቸውም ሰው "ወካይ" ተብሎ ስሚጠራ ሌላ ሰው ወኪል በመሆን በሌላ ሰው ስም የሚሰራ በሚሆንበት ጊዜ ወኪሉ የወካዩ በቋሚነት የሚሠሩ ድርጅት ነው የሚባለው፤

ሀ/ በወካዩ ስም በቋሚነት ውሎችን የሚደራደር፣ ወይም

ለ/ ቢወካዩ ስም የንግድ ዕቃዎችን ለማስረከብ አስማችቶ የሚይዝ ከሆነ ነው።

፲). በዚህ አንቀጽ "ራሱን ችሎ የሚሠራ ወኪል" ማለት በሚወክለው ሰው ቁጥጥር ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚሠራ ደላላ፣ የኮሚሽን ወኪል ወይም ሌላ ወኪል ሲሆን፣ የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነታቸው ራሳቸውን ችለው ከሚሠሩ ሰዎች የተለየ የሆነውን በብቸኝነት ወይም በቃነኛነት ለአንድ ሰው ወኪል በመሆን የሚሠሩትን አይጨምርም።

፲፩). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም **"የቴክኒክ አገልግሎት"** ማለት የቴክኒክ፣ የአስተዳደር ወይም የምክር አገልግሎት ባህሪ ያላቸውን አልግሎቶችን የሚያካትት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ) የሂሳብ አያያዝ፤

ለ) የኦዲት፤

ሐ) የኢኮኖሚና አንቨስትመንት

መ) የፋይናንስ፤

ሠ/ የህግ፤

ረ) የአስተዳደር፤

ሰ) የኢንጂነሪንግ፤

ሸ) የአርኪቴክቸር፤

ቀ) የቅየሳ፤

በ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፤

ተ) ለጤና ባለሙያዎች

ቸ) ማህበራዊ ጉዳይ፣ ወይ በሌላ ተመሳሳይ መስክ የሚሰጥ የሙያ አገልግሎት፤"

፰. ነዋሪነት

፩). የሚከተሉት የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ናቸው፡፡

ሀ/ ነዋሪ የሆነ ግለሰብ፣

ለ/ ነዋሪ የሆነ ድርጅት፣

ሐ/ የክልሉ መንግስት እንዲሁም ማናቸውም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞን አስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደር

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፤ አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ፭፩ (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ፣

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት "የተያዘው የግብር ዓመት" ተብሎ ለሚጠቀሰው ለአንድ የግብር ዓመት ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ባለፈው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ ፣ተያዘው የግብር ዓመት እንደነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ከጀመረበት ቀን አንስቶ ነው፡፡

፬). አንድ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት በተያዘው የግብር ዓመት ነዋሪ ሆኖ፤ ነገር ግን በሚቀጥለው የግብር ዓመት ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ፤ ፣ተያዘው የግብር ዓመት እንደ ነዋሪ ሆኖ የሚቆጠረው ግለሰቡ ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከኖረበት ቀን በፊት ላለው ጊዜ ነው፡፡

፭). አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ወይም የተመሠረተ እንደሆነ፣

ለ/ ወሳኝ የሆነ አመራር የሚያካሂድበት ሥፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እንደሆነ፣ ነው፡፡

፮). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ነው፡፡

፯). ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚባለው ማንኛውም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

፱. የገቢ ምንጭ

፩). አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ክፍያው የሚፈጸምበት ሥፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ፣ ወይም

ለ/ የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ መንግሥት ወይም በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ክፍያው ለተቀጣሪው ከተፈፀመ፣

፪). በቋሚነት ቢሠራ ድርጅት አማካይነት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያገኘውን ገቢ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያፈራው የንግድ ሥራ ገቢ በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ገቢ ይሆናል።

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅቱ አማካይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ ሲሆን፣

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካይነት ከሚሸጣቸው እቃዎች ወይም ሸቀጦች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ እቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ኢትዮጵያ ውስጥ በመሸጥ የሚያገኘው ገቢ፣

ሐ/ በኢትዮጵያ ወስጥ ነዋሪ ያልሆነው ሰው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ከሚያከናውናቸው ማናቸውም የንግድ ሥራዎች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ በማከናወን የሚያገኘው ገቢ፣

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣(፪) እና (፫) የተመለከተው ቢኖርም፣ የሚከተሉት ገቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የመነጩ ገቢዎች ናቸው፡-

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት ለአንድ ሰው የሚከፍለው የትርፍ ድርሻ፣

ለ/ የሚከተሉትን ንብረቶች በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

፩. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም

፪. በአንቀጽ ፶፯ መሠረት ግብር የሚከፈልበት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ ንብረት፣

ሐ/ የሚከተሉትን ንብረቶች በመሸጥ ወይም ባመለወጥ የሚገኝ ገቢ፡-

፩. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት፣

፪. ከሃምሳ በመቶ (50%) በላይ በሚሆነው በንብረቱ ዋጋ ላይ ያለው ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለመንግሥት በአንድ ወይም [illegible] በሆኑ

የተዛመዱ ድርጅቶች የተያዘ በሚሆንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለ ጥቅም፣

ፒ. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ያወጣው አክሲዮን ወይም ቦንድ፣

መ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መድን ለተገባለት አደጋ (ስጋት) የሚከፈል የመድን አረቦን፣

ሠ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወን የመዝናኛ ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የዕድል ሙከራዎችን በማሸነፍ የሚገኝ ገቢ፣

ሰ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት፡-

ሸ. በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት ውጭ ሀገር ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ ያወጣውን ወጪ ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው የሚፈጽመው ክፍያ፣

ቀ. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ወስጥ ለሚያካሂደው የንግድ ሥራ የሚፈጽመው ክፍያ፣

ሸ). በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ በክልሉ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ይቆጠራል።"

፯. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩). ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በግል የሚያርሱ ገበሬዎችን ሳይጨምር በፌደራሉ ሕገ መንግስት ለብሄራዊ ክልሉ ተሰይቶ በተሰጠው የግብር ሰልጣን በሚሸፈኑ ግብር ከፋዮች ላይ ነው።

፪) ማንኛውም ሰው በክልሉ ውስጥ በሚያገኘው በማናቸውም ገቢ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፰. <u>የገቢ ሠንጠረጐች</u>

፩). በዚህ አዋጅ የተደነገገው የገቢ ግብር በሚከተሉት ሠንጠረጐች መሠረት ይከፈላል።

ሀ/ ሠንጠረዥ "ሀ" ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣

ለ/ ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፣

ሐ/ ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ

መ/ ሠንጠረዥ "መ"ሌሎች ገቢዎች፣

ሠ/ ሠንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች፣

፪). የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፬(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው በዚያው ሠንጠረዥ ሥር የዓመቱን ግብር ይከፍላል።

፱. <u>የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ</u>

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

ክፍል ሁለት

ሠንጠረዥ "ሀ"፣ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

፲. <u>ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል</u>

፩). በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፹፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚያገኘው ጠቅላላ የወር ወይም የወሩ ከፊል ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተወሰኑት ምጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ ወር ግብር ይከፍላል።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከመቀጠር በሚገኝ ወርሀዊ ገቢ ላይ የሚጣለው የገቢ ግብር ተቀጣሪው በአንድ ወር ውስጥ በሚያገኘው ጠቅላላ ወርሃዊ ወይም በወሩ ከፊል ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነውን ምጣኔ መሠረት በማድረግ ይሰላል።

፫). ተቀጣሪው በመቀጠር የሚገኘውን ገቢ ለማግኘት የሚያወጣው ማንኛውም ወጭ በተቀናሽ ሊያዝለት አይችልም፡

፬). ለዚህ ሠንጠረዥና ለዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፰ አፈጻፀም ሲባል፤ በነሐሴና በጳጉሜ ወራት የሚከፈለው የቅጥር ገቢ ተደምሮ እንደ የአንድ ወር ደመወዝ ግብር ይከፈልበታል።

፭) በአንድ ተቀጣሪ ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬ (፩) ድንጋጌ ተፈጻሚ የተደረገ እንደሆነ በመቀጠር በተገኘው ገቢ ላይ ተቀጣሪው የከፈለው ታክስ የመጨረሻ ይሆናል። ቀጣሪው በአንቀጽ ፹፰ መሠረት ከተቀጣሪው የሚፈለገውን የገቢ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ ግብሩ እንደተከፈለ ይቆጠራል።

፲፩. በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ምጣኔዎች

በመቀጠር በሚገኝ ወርሃዊ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈጻሚ የሚሆኑት ምጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፦

በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ (ብር)		በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን መጣኔ
ከብር	አስከ ብር	
0	2,000	0%
2,001	4,000	15%
4,001	7,000	20%
7,001	10,000	25%
10,001	14,000	30%
ከ14,000	በላይ	35%

፲፪. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከመቀጠር የሚገኙ ገቢዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ ሠራተኛው ካለፈው፣ አሁን ካለው ወይም ወደፊት ከሚመጣው ቅጥር ጋር በተያያዘ የተቀበለው ደመወዝ፣ ምንዳ፣ አበል፣ ጉርሻ፣ ኮሚሽን፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማበረታቻ ስጦታ ወይም ሌላ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ፣

ለ/ ያለፈን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊትን ቅጥር አስመልክቶ ሠራተኛው የሚቀበለው የዓይነት ጥቅማ ጥቅም ዋጋ፣

ሐ/ ተቀጣሪው ከሥራ ሲቀነስ፣ ሥራውን ሲለቅ ወይም ሥራውን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብን ጨምሮ የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ ይሰምምነት ወይም በዳኝነት ውሳኔ መሠረት የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን፣

፪). በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ካግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም።

፫).ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ በቀጣሪው የተከፈለው የግብር መጠን ተቀጣሪው ከመቀጠር ከሚያገኘው ግብር ሊከፈልበት የገንዘብ መጠን ላይ ተደምሮ ግብሩ ይሰላል፡

፬). የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከደመወዝ ሌላ በዓይነት የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች ዋጋ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፭ መሰረት አልፎ አልፎ የሚገኝ ተጠቃለው የሚከፈሉ ገቢዎች የሚወሰንበትንና ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ደንብ ያወጣል፡፡

፭). የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ መብት የሌላቸውን ሠራተኞችን በሚመለከት የክልሉ ገቢዎች ቢሮ መረጃ ሲጠይቅ መረጃውን ለገቢዎች ቢሮ የማስተላለፍ ኃላፊነት ይኖርበታል።

፮). በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጭ ሠራተኞች ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ፈቃድ የመስጠት ወይም የማደስ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም የመንግሥት አካላት ፈቃድ የተሰጠ ወይም እድሳት የተደረገ ስለመሆኑ ወዲያውኑ ለገቢዎች ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው።

፯). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሰረት የሚሰጠው ማሳወቂያ የሠራተኛውን ሙሉ ስም፣ በኢትዮጵያ የሚገኘውን አድራሻቸውን፣ የአሠሪውን ስም፣ የሥራ ፈቃዱን ዓይነት ፣የቆይታ ጊዜ፣ ደመወዝ እና ሌሎች የዓይነት ጥቅማጥቅሞች እንዲሁም በገቢዎች ቢሮ ሊጠየቅ የሚችል ማንኛውንም ሌላ ተገቢ መረጃን ማካተት አለበት።

ክፍል ሦስት

ሠንጠረዥ "ለ" ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

፲፫. በቤት ኪራይ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል

፩). ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ በተመለከተው መጣኔ ወይም መጣኔዎች መሠረት በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

፪). በግብር ዓመቱ አንድ ግብር ከፋይ ከቤት ኪራይ በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ሥር የተመለከቱትን ምጣኔዎች ግብር በሚከፈልበት ዓመታዊ ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

፫). ይህ ሠንጠረዥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ መሠረት የኪራይ ገቢ ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፲፬. የኪራይ ገቢ ግብር ምጣኔዎች

፩).. በድርጅቶች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የግብር ምጣኔ ፴ በመቶ (ሰላሳ በመቶ) ነው፡፡

፪). በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው።

ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ በዓመት		የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ
ከብር	አስከ ብር	
0	24,000	0%
24,001	48,000	15%
48,001	84,000	20%
84,001	120,000	25%
120,001	168,000	30%
ከ168,000	በላይ	35%

፲፩. ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ

፩). የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ የኪራይ ገቢ ነው የሚባለው ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ ቤት በማከራየት ካገኘው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀደው ጠቅላላ ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀረው ገቢ ነው።

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ የኪራይ ዋጋ ጭማሪን ወይም ተመሳሳይ ክፍያዎችን ጨምሮ፣ በኪራይ ውሉ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ የሚያገኘው ጥናቸውም የገንዘብ መጦን፣

ለ/ በኪራይ ውሉ መሠረት ተከራዩ አከራዩን በመወከል በግብር ዓመቱ ለሌሎች የሚከፍሏቸው ክፍያዎች፣

ሐ/ ግብር ከፋዩ ጉዳቱን ለማስተካከል ያልተጠቀመበት እና በቤቱ ላይ ሊሚደርሰው ጉዳት ማስተካከያ ይሆን ዘንድ የያዘው እና በግብር ዓመቱ ለግብር ከፋዩ ገቢ የተደረገው ማንኛውም ቦንድ፣ ዋስትና ወይም ተመሳሳይ የገንዘብ መጠን፣

መ/ ለግብር ከፋዩ ከሚከፈለው ኪራይ በተጨማሪ በኪራዩ ውል መሠረት ተከራዩ ራሱ ለቤቱ እድሳት ወይም ማሻሻያ የሚያወጣው ገንዘብ፣

፫).ግብር ከፋዩ ቤቱን ያከራየው ከዕቃዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ፣ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ዕቃዎቹ የተገኘውን የኪራይ ገቢም ያጠቃልላል።

፬). ግብር ከፋዩ ቤት በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከገቢ ግብር ነጻ የሆነን ገቢ አይጨምርም፡

፭). በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጭዎች በተቀናሽ ይያዛሉ፡-

ሀ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፣

ለ/ ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ ማደሻ፣መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ የሚሆን ክቤት፣ ከቤት ዕቃ እና ከመሳሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ ሃምሳ በመቶ፣

፮). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ በማናቸውም ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት የሂሳብ መዝገብ የመያዘ ግዴታ ላለባቸው ግብር ከፋዮች ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም።

፯) የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ የዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ ገቢውን ለማግኘት የወጣና በታክስ ከፋዩ የተከፈለ ወጪ ተቀናሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ወጪ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ/ ቤቱ ያረፈበት መሬት ኪራይ፣

ለ/ የጥገና ወጭ፣

ሐ/ የቤቱ፣ የቤት ዕቃዎችና የመሣሪያዎች የእርጅና ቅናሽ፣

መ/ ወለድና የመድን አረቦን፣

ሠ/ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፣

፰). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም **"ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ"** ማለት ለማናቸውም አገልግሎት ክሚውል ህንጻ፣ ከመኖሪያ ቤት ፣ ለመጋዘን አገልግሎት ከሚውል ህንጻ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ሲሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚገነባቸውን የኢንዱስትሪ መሰረተ ልማቶች እና በካፒታል እቃ ኪራይ ንግድ ሥራ መሰረት የንግድ ሥራ ህብት ሆነው የሚከራዩ ህንጻዎችን ወይም ግሪን ሀውስ እና በመጋዘን ውስጥ እቃ የሚያከማቹ ሰዎች የሚከፍሉትን ክፍያ አይጨምርም።

፲፮. <u>የተከራይ አከራዮች</u>

፩.) የተከራይ አከራይ በግብር ዓመቱ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው የሚባለው የተከራይ አከራዩ በግብር ዓመቱ ከተቀበለው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ ላይ ለዋናው አከራይ የሚከፍለው ኪራይ እንዲሁም ገቢውን ለማግኘት ያወጣቸው ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ነው።

፪). ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ሳይከፍል ቢቀር ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።

፲፯. <u>የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማሳወቅ</u>

፩). ለኪራይ የሚሰራ ቤት ተሰርቶ እንዳለቀ ወይም ቤቱ እንደተከራየ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የቤቱ ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም የተከራየ መሆኑን ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው ስም፣ አድራሻና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ቤቱ ለሚገኝበት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የአካባቢ አስተዳደር ማስታወቅ አለባቸው።

፪) የቀበሌው አስተዳደር እና የአካባቢው አስተዳደር በማስታወቂያው መሠረት የተገኘውን መረጃ ለባለሥልጣኑ መግለጽ አለባቸው።

ክፍል አራት

ሠንጠረዥ "ሐ" ከንግድሥራ የሚገኝ ገቢ

ምዕራፍ አንድ

ከንግድ ሥራ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል

፲፰. <u>በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ግብርን ስለመጣል</u>

፩). በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዓመት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ በተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች መሠረት የንግድ ገቢ ግብር ይከፍላል።

፪). አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት የሚከፍለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰላው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ የተመለከተው ምጣኔ ወይም ምጣኔዎች በግብር ከፋዩ የግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ነው።

፲፱. በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ምጣኔዎች

፩). በድርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ የግብር መጣኔ ሰላሳ በመቶ (30%) ነው።

፪). በጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ ግብር የሚከፍሉ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን ሳይጨምር በግለሰብ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው

ከንግድ ስራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በአመት		የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ
ከብር	አስክ ብር	
0	24,000	
24,001	48,000	15%
48,001	84,000	20%
84,001	120,000	25%
120,001	168,000	30%
ከ168,000	በላይ	35%

፫). በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተደነገገው ቢኖርም በሀጋዊ መንገድ የተመዘገበ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ በማናቸውም የሕግ ቅርጽ ቢቋቋምም በድርጅት ደረጃ የሚያገኘው ገቢ ግብር አይከፈልበትም።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ለባለአክሲዮኖቹ ከሚያከፋፍለው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ መሰረት የትርፍ ድርሻ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት። የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣውደንብ ይወሰናል።

፭). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንቨስትመንት ፈንድ ድርጅቱ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ሌሎች ግዴታዎች ተፈጻሚ ይሆንባቸዋል።

፮). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚገደዱ ወይም በፈቃደኝነት የሚይዙ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ግብር የሚከፍሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር በተመለከቱት መጣኔዎች መሠረት ይሆናል።

፯). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራና ስልጠና ቢሮ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል

፵. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ

፩). የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ዓመታዊ የንግድ ሥራ ገቢ ነው የሚባለው ከንግድ ሥራ ከተገኘ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ የተፈቀዱት ወጪዎች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ የሚገኘው የገቢ መጠን ነው።

፪) በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች፣ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች እና ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ የሚደረጉ ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ የሚወሰነው ግብር ከፋዩ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት በሚያዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም ገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል።

፵፩. የንግድ ሥራ ገቢ

፩). የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአንድ የግብር ዓመት የአንድ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ከፋይ የንግድ ገቢ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ ዕቃዎችን ቢመሸጥና በመለወጥ እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ሥራ ያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ መጠን፣

ለ/ ለንግድ የሚውል ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ የገንዘብ መጠን፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ተደርጎ የሚወሰድ ሌላ ማንኛውም የገንዘብ መጠን፣

፪). ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገን ገቢ አይጨምርም።

፫). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተው የንግድ ሥራ ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ከንግድ ሥራ ሀብቱ የመዝገብ ዋጋ በላይ የሆነው የንግድ ሥራ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ከተላለፈው ሀብት የተገኘው ገቢ ነው።

፬). አንድ የንግድ ሥራ ሀብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ፦

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭(ሰ) መሠረት በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የሚካተተውን የንግድ ሥራ ሀብትን በማዕተላለፍ የሚገኘውን ገቢ ለንግድ ሥራው ሀብት የተደረገው ወጪ ከንግድ ሥራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ሲሆን፣

ለ/ ከወጪው በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአንቀጽ ፶፰ መሠረት ግብር ይከፈልበታል።

፳፪. <u>ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ</u>

፩). ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟላ የንግድ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል፦

ሀ/ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ በመደበኛነት የሚከናወን ከሆነ፤

ለ/ ፈጣሪው ድርጅት ከሆነ፤ እና

ሐ/ የሂሳብ መዝገብ የሚያዙ ከሆነ ወይም ከንግድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉለት ከሆነ።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ፣ ገቢው እንደ ሌላ ገቢ ተመድቦ በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚጣልበት ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፫). የገቢዎች ቢሮ የዲጂታል ይዘት ፈጠራ የንግድ እንቅስቃሴ መሆኑን ለመወሰን መመሪያዎች ያወጣል፤ በተለይም የገቢውን ሞጠን፣ የግብይቶችን ብዛት፣ የይዘቱን ዓይነት እና የንግድ ዓላማውን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

፬). በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ለሚኖሩ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያዎችን የሚያመቻች ማንኛውም የኦንላይን መድረክ፣ ዓመታዊ ገቢያቸው ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወሰነው ገደብ በላይ ከሆነ ለእያንዳንዱ ፈጣሪ ያገኙትን ጠቅላላ ገቢ በየዓመቱ ለገቢዎች ቢሮ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፭). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት በኦንላይን መድረክ ሪፖርት የተደረገም ይሁን ያልተደረገ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ማንኛውም ገቢን በተመለከተ፣ ገቢው በደረሰው ሰው በዓመታዊ የገቢ ግብር ማስታወቂያው ላይ መገለጽ አለበት።

፫) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ ከተወሰነው ገደብ በላይ ገቢ የሚያገኝ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማግኘት እና ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን የግብር ግዴታዎችን መወጣት አለበት።

፷፫. <u>አማራጭ አነስተኛ ግብር</u>

፩). በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ማናቸውም አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም፤ ማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው ግብር በሚወሰንበት የግብር አመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባው ግብር በዚሁ የግብር አመት ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከ2.5% (ከሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በታች ከሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር መክፈል አለበት።

፪). በዚህ አንቀጽ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚከፈለው በሚከተለው የማስከፈያ ምጣኔ ይሆናል፦

ሀ) የማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው አመታዊ ጠቅላላ ገቢ 2.5%፤ ወይም

ለ) ዋጋቸው የተወሰነ እቃዎችን አቅራቢ ሰው ወይም ድርጅትን በሚመለከት የኮሚሽን ገቢው 2.5%፤

፫). በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው አማራጭ አነስተኛ ግብር በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ መሰረት ከሚከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።

፬). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀጽ ፵፱ መሰረት በጠቅላላ ገቢው ላይ ግብር በሚከፍል ግብር ከፋይ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፭). በዚህ አንቀጽ መሰረት ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ሊከፍል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ላይ የሚቀነሰው ቢሚከተለው አኳኋን ይሆናል፦

ሀ) እስከ ፭ (አምስት) አመታት ድረስ፤

ለ) በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ መሰረት ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ የሚቀነሰው ሂሳብ በዚህ አንቀጽ መሰረት ሊከፈል እስከሚገባው አማራጭ አነስተኛ ግብር ድረስ ሆኖ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት የተከፈለውን ተቀናሽ የተደረገበት የንግድ ትርፍ ግብር ሳይጨምር ይሆናል

፮). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አ ንቀጽ ፪ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሚከተሉት ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ተደርገዋል፦

ሀ) በኪሳራ ምክንያት መፍረስ ላይ ያለ ድርጅት፤ እና

ለ) በእዳ ማሸጋሸግ ላይ ያለ ድርጅት

፰). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ህግ መሰረት የግብር እፎይታ በተሰጠው ሰው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል። ስለሆነም አማራጭ አነስተኛው ግብር የተሰጠው ማበረታቻ ተቀንሶ ሊከፈል በሚገባው የገቢ ግብር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፰). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-

ሀ) **"አመታዊ ጠቅላላ ገቢ"** ማለት በግብር አመቱ ከተከናወነ የእቃ ሽያጭ እና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ነው

ለ) **"የኮሚሽን ገቢ"** ማለት በህግ ወይም ውልን ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል በጸደቀ ውል በተወሰነው መሰረት ከአንድ እቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ሰጪው የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡

(ሐ) **"ዋጋው የተወሰነ ድርጅት"** ማለት እቃዎችን የሚሸጥበት ወይም አገልግሎትን የሚቀርብበት ዋጋ በውል ወይም በመንግስት አካል የተወሰነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ድርጅት ነው

<u>፳፬. ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች</u>

፩). የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽ የሚያዙት ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

ሀ/ በንግድ ሥራው ገቢው ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፤

ለ/ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በተመለከተው መሠረት የተሠላ በግብር ዓመቱ በግብር ከፋዩ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ የወጣ ወጪ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ በሚወሰነው መሠረት የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ሥራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣

መ/ ግብር ከፋዩ የንግድ ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ሀብትን ሲሸጥ ወይም ሲለውጥ የሚገጥመው ኪሳራ፣

ሠ/ ለግብር ዘመኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት የሚፈቀድ ሌላ ማናቸውም ወጪ፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጉዳዮች ቢሮ

፪). ግብር የሚከፈልበት ሃብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ካልሆነ በስተቀር፣ ግብር የሚከፈልበት ሃብት በሚተላለፍበት ጊዜ ሰሚደርስ ኪሳራ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) (መ) ግን ተፈጻሚ አይሆንም።

፫). ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(መ) አፈጻፀም፤ የንግድ ሀብትን በማስተላለፍ የሚደርስ ኪሳራ የሚባለው ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ በሚበልጠው የገንዘብ ልክ ነው።

፳፭. <u>የወለድ ወጪ</u>

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ እንደተጠበቁ ሆነው፤ ግብር ከፋዩ የወሰደውን ብድር ወይም ሌላ ዕዳ ወይም ያደረገውን ስምምነት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ተግባር ያዋለው እስከሆነ ድረስ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከፈለው ወለድ የግብር ከፋዩ የግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ እንደወጪ ይያዝለታል።

፪) ለሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይፈቀድም፡

ሀ/ ወለዱ በብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ ምጣ ፪ በመቶ (2%) የሚበልጥ ከሆነ በተቀናሽ አይያዝም፤ ነገር ግን ወለዱ ፡

፩. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ለተሰጠው የፋይናንስ ተቋም ፣

፪. በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሰዎች ብድር እንዲሰጥ ለተፈቀደለት የውጭ ሀገር ባንክ የተከፈለ ወይም የሚከፈል ከሆነ በተቀናሽ ይያዛል።

ለ/ የወለዱ ገቢ ግንኙነት ባለው ሰው የንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ ካልተካተተ በስተቀር፣ አንድ ግብር ከፋይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ግንኙነት ላለው ሰው የከፈለው ወይም የሚከፍለው ወለድ፣

፳፮. <u>ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች</u>

፩). የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ያደረገው ስጦታ ተቀናሽ የሚደረገው ስጦታው ለሚከተሉት የተደረገ ሲሆን ነው፦

ሀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ለተመለከተው የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማኅበር፣ ወይም

ለ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የየክልል መስተዳድር ምክር ቤት ወይም ካቢኔ ባፀደቀው ጥሪ መሰረት የአገሪቱን አንድነት ዓ[illegible]

ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ወይም የገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ለተዘረዘሩ ማህበራዊ ስራዎች የሚውል ከሆነ ነው።

፪). በዚህ አንቀጽ መሰረት ለግብር ከፋዩ የሚፈቀደው ጠቅላላ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመት ገቢ ፲% (አስር በመቶ) መብለጥ የለበትም። ሆኖም የገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ለተወሰኑ መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች የሚደረገው ድጋፍ ከዚህ መጠን ከፍ እንዲል ሊፈቀድ ይችላል።

፫). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማኅበር" በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

፵፯. <u>የእርጅና ቅናሽ</u>

፩). የግብር ከፋዩን በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፍልበትን ገቢ ለመወሰን ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው እና ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ሰማድረግ ይፈቀድለታል፡

፪). የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሀብቶች በየግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፫). አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸውን ሀብቶች ያልተጠቀመ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ሆኖ፣ የንግድ ሀብቱ ጥቅም ላይ ያልዋለበት ዓመት ሂሣብ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ከተቀነሰ በኋላ ነው።

፬). አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት እና ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው ሀብት በከፊል የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት የተጠቀመበት እንደሆነ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚደረገው ማስተካከያ ከግምት ውስጥ ገብቶ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የንግድ ሥራ ገቢውን ለማግኘት በዋለው መጠን የሚሰላ ይሆናል።

ሰ/. "ዋጋው የሚቀንስ ሀብት" ማለት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ግዙፋዊ ሀልዮት ያለው የሚንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ማሻሻያንም ይጨምራል፡፡

፩. ከአንድ ዓመት የሚበልጥ የአገልግሎት ዘመን ያለው፣

፪. በእርጅና ወይም ጊዜው በማለፍ ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ የሚችል፤

፫. በከፊል ወይም በሙሉ የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋለ፤

ሐ/. "በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ" ማለት ቤት፣ ወይም ሌላ የቤቱ አካል የሚሆን ወይም ከቤቱ ጋር ለዘለቄታው የተያያዘ በቤቱ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጭማሪ ወይም ለውጥ ሲሆን መንገድን፣ መጋቢ መንገድ፣ የመኪና ማቆሚያ አጥር ወይም ግንብን ይጨምራል፡፡

፰). የንግድ ስራ ሀብት በባል ወይም በሚስቱ ስም ሆኖ የንግድ ስራው ሀብት ባለቤትነት ከሁለቱ በአንዱ ስም ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የእርጅና ቅናሽ ወጪ ሊያዝላቸው የሚችለው ባልና ሚስት ለለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ህጋዊ የሰነድ ማስረጃ ሲያቀርቡ ብቻ ይሆናል፡፡

፳፰. <u>ኪሳራን ስለማሸጋገር</u>

፩). በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈቀደውን ተቀናሽ ሳይጨምር፣ ለግብር ዓመቱ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ግብር ከፋዩ በግብር ዘመኑ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከበለጠ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን ግብር ከፋዩ የደረሰበት ኪሳራ ይሆናል፡፡

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ኪሳራ ካጋጠመው፣ በግብር ዓመቱ የደረሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ለማሸጋገር ይችላል፤ ስለሆነም የግብር ከፋዩ የሚቀጥለው ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የተሸጋገረው ኪሳራ በተቀናሽነት ይያዛል፡፡

፫). ግብር ከፋዩ ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሙሉ በሙሉ መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ያልተቀነሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ማሸጋገር እና የተካካሰውን መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተገለጸው መሠረት በዚያው የግብር ዓመት ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ በመቀነስ ኪሣራው ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ተደርጐ እስከሚያልቅ ድረስ ማሸጋገር የሚችል ሲሆን ነገር ግን ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሣራ ኪሣራው ከተከሰተበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠሩ አምስት የግብር ዓመታት በላይ ማሻገር አይችልም፡፡

፬). ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ለኪሳራ የተዳረገባቸው ሁለት ዓመታት ያሉ እንደሆነ እና እያንዳንዱ ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተሸጋገረ እንደሆነ ግብር ከፋዩ በንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ሌላ ማንኛውንም ተጨማሪ ኪሳራ እንዲያሸጋግር ሊፈቀድለት አይችልም።

፭). ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ መሠረት ኪሳራ ሊያሸጋግር የሚችለው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሆናል።

፷፱. <u>ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች እና ኪሳራዎች</u>

፩). በዚህ አዋጅ ከተደነገገው በስተቀር የሚከተሉት ወጭዎች በተቀናሽ አይያዙም፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱(፩)(ሐ) ከተደነገገው በስተቀር የካፒታልነት ባህርይ ያላቸው ወጪዎች፣

ለ/ የኩባንያ አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ፣

ሐ/ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ፲፭% (አሥራ አምስት መቶኛ) በላይ የሚደረግ የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ ፣

መ/ የአክሲዮን ድርሻ እና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል፣

ሠ/ በመድን፣ በካሳ ወይም በዋስትና ውል መሠረት የተመለሰ ወይም ሊመለስ የሚችል ወጪ ወይም ኪሳራ፣

ረ/ ማንኛውንም ሕግ ወይም ውል በመጣስ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ወይም የሚከፈል ካሳ፣

ሰ/ ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ የሚይዘው በወቅቱ ወጪ ያልተደረገ ነገር ግን ለወደፊት የግብር ዓመት ለሚከሰቱ ወጪዎች ወይም ኪሳራዎች መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ የሚያዝ ገንዘብ ወይም የመጠባበቂያ ሂሣብ፣

ሸ/ በዚህ አዋጅ ወይም በውጭ ሀገር የታክስ ሕግ መሠረት የተከፈለ የገቢ ግብር ወይም ተመሳሳይ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

ቀ/ መሥሪያ ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኝ ተቀጣሪ ከተቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ፲% (አሥር በመቶ) ቢላይ የሚከፈል የኃላፊነት አበል፣

በ/ ከሚከተሉት በስተቀር ለመዝናኛ የሚወጣ ወጪ፣

፩. የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት ሲሆን፤ ወይም

፪. ቢሮው በመመሪያ ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በማሰድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ ወይም በግብርና ሥራ ዮተሠማራ ቀጣሪ ሠራተኞቹን ለማዝናናት የሚያወጣው ወጪ፤

ተ/ በአንቀጽ ፮፪ ከተመለከተው ውጪ የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

ቸ/ ግብር ከፋዩ አንድን የንግድ ሃብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ የሚደርስ ኪሳራ፣

ኀ/ ግብር ከፋዩ ለራሱ የሚያወጣው ወጪ፤

ነ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ተቀናሽ የማይደረጉ ናቸው የተባሉ ወጪዎች፣

ኘ/ ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከአንድ የባንክ ሂሳብ ወደ ሌላ የባንክ ሂሳብ እና/ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈጸሚያ መንገዶች ገንዘብ ከማስተላለፍ ውጪ በአንድ ቀን ውስጥ ለአንድ ሰው ከብር 50,000 (ሀምሳ ሺህ ብር) በላይ በሆነ ጥሬ ገንዘብ የፈጸመው ወይም የፈጸማቸው ክፍያዎች፤

አ/ የክተማ አገልግሎት ክፍያዎች ፤ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

፪) በዚህ አንቀጽ "መዝናኛ" ማለት ለማንኛውም ሰው የሚቀርብ ምግብ፣ መጠጥ፣ ትንባሆ፣ ማረፊያ፣ መደለቻ ወይም ማናቸውም ዓይነት መስተንግዶ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የታክስ ሂሳብ አያያዝ

፴. <u>የሂሳብ ዓመት</u>

፩). ይህ አንቀጽ በሚከተሉት ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱(፳፫)(ሀ) ለግብር ዓመት በተሰጠው ትርጉም መሠረት የራሱን የሂሳብ ዓመት እንደ ግብር ዓመት አድርጎ እንዲጠቀም ፈቃድ ለተሰጠው ግለሰብ ግብር ከፋይ፣

ለ/ ድርጅት

፪). ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ለሚሆንበት ግብር ከፋይ የሂሳብ ዓመት ነው የሚባለው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ የፋይናንስ ሂሳብ ሚዛን በሚዘጋበት ጊዜ የሚጠናቀቀው የአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ነው

፫). ማንኛውም ግብር ከፋይ ከገቢዎች ቢሮ አስቀድሞ በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝና ገቢዎች ቢሮ የሚያስቀምጣቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ሳያሟላ የሂሳብ ዓመቱን ለመቀየር አይችልም።

፬) ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት ከተሰጠው ፈቃድ ጋር የተያያዘውን ማንኛውንም ቅድመ-ሁኔታ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዘው ይችላል።

፭). የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት በንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም (፬) መሠረት የተለወጠ እንደሆነ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ባለው የግብር ዓመት እና አዲሱ የግብር ዓመት በሚጀምርበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ "የመሸጋገሪያ ዓመት" በመባል የሚታወቅና ራሱን የቻለ የግብር ዓመት ተደርጎ ይወሰዳል።

፮). የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት ከበጀት ዓመቱ ጋር የማይገጥም በሚሆንበት ጊዜ ለሂሳብ ዓመቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ በሂሳብ ዓመቱ ውስጥ በሚጠናቀቀው የበጀት ዓመት ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ ነው።

፴፩. የታክስ ሂሳብ አያያዝ ዘዴን ስለመለወጥ

፩). ግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን ለመለወጥ ለገቢዎች ቢሮ የጽሁፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፣ ገቢዎች ቢሮ ለውጡ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በትክክል ለማስላት የሚያስፈልግ መሆኑን ሲያምንበት ግብር ከፋዩ የሂሳብ ዘዴውን ለመለወጥ ያቀረበውን ማመልከቻ መቀበሉን በጽሁፍ ሊያሳውቀው ይችላል።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ በሚለወጥበት የግብር ዓመት የግብር ከፋዩ የግብር ከፋይ ደረጃም የሚለወጥ ከሆነ፣ የግብር ከፋዩ ገቢ ሳይመዘገብ እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገብ ለማድረግ ስገቢ ርዕሶች፣ በተቀናሽ ወጪዎች ወይም በታክስ ማካካሻ ሂሳቦች ላይ ከለውጡ ጋር በተያያዘ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ አለበት።

፴፪. የማይሰበሰቡ ዕዳዎች

፩). በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የማይሰበሰበው ዕዳ ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት ይያዝለታል፣

ሀ/ ከማይሰበሰው ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሂሳብ ቀደም ሲል የግብር ከፋዩ የንግድ ገቢ ሆኖ ተይዞ ከሆነ፣

ለ/ ዕዳው ወይም የዕዳው የተወሰነ የገንዘብ መጠን ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ላይ ሲሰረዝ፣

ሐ/ ዕዳውን ለማስመለስ የህግ እርምጃ ተወስዶ ዕዳው ሳይመለስ ሲቀር፣

፪). ለግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ መሠረት በግብር ዓመቱ የሚፈቀደው የተቀናሽ የገንዘብ መጠን በግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ከተሰረዘው የዕዳ መጠን መብለጥ አይኖርበትም።

፫). ይህ አንቀጽ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው የፋይናንስ ተቋማት ተፈጻሚ አይሆንም።

፴፫. የፋይናንስ ተቋማት እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚያወጣው የገቢ ግብር ደንብ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚወስኑ ድንጋጌዎችን ሊይዝ ይችላል፦

ሀ/ የፋይናንስ ተቋማት የሚይዙት የኪሳራ መጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ የሚደረግበትን አኳኋን፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት * የርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት *
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት * ገቢዎች ቢሮ *
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ሰ/ የሕይወት መድን ኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ሳይጨምር፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ከሚያወጡዋቸው ጊዜያቸው ካላለፈባቸው የኢንሹራንስ ዋስትናዎች ጋር በተያያዘ የሚይዙት የመጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣

ሐ/ የሕይወት መድን ኩባንያዎች የተጣራ ገቢ የሚሠላበትን ሁኔታ፣

፴፬. ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ውሎች

፩). ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተክፋይ ሂሳብ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ከተዋዋለው የረዥም ጊዜ ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሠረት በማድረግ ገቢውን በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ሲያካትት ወጪውም በዚያው መቶኛ ልክ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል።

፪). በግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገው ውል ውስጥ በግብር ዓመቱ የተጠናቀቀው በመቶኛ የሚወሰነው በግብር ዓመቱ የሚኖረውን ለውጥ ጨምሮ ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ የወጣውን ወጭ ከአጠቃላይ የውሉ ወጪ ግምት ጋር በማነጻፀር ይሆናል።

፫). ግብር ከፋዩ ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ በውሉ የመጨረሻ ዓመት ኪሳራ የደረሰበት እና በአንቀጽ ፳፰ መሠረት ኪሳራውን እንዲያሸጋግር የተፈቀደለት ቢሆንም ኪሳራውን ማሸጋገር ያልቻለ ሆኖ በውሉ ዘመን መጨረሻ በክልሉ የንግድ ሥራ መሥራት ያቆመ እንደሆነ ይህ ግብር ከፋይ የደረሰበት ኪሳራ ወደ ኋላ ተመልሶ በአምናው የግብር ዘመን በተቀናሽነት እንዲያዝለት ይደረጋል።

፬). ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት ወደ ኋላ ተመልሶ መሉ በሙሉ በተቀናሽ ወጪነት እንዲያዝ ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣ ያልተቀነሰው ኪሳራ ወደኋላ ተመልሶ ወደአቻምናው የግብር ዓመት የሚሸጋገር ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል።

፭). ግብር ከፋዩ በረዥም ጊዜ ውል ኪሣራ ደርሶበታል የሚባለው የሚከተሉት ሁለት ቅድመ-ሁኔታዎች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል።

ሀ/ የተጠናቀቀውን ሥራ በመቶኛ ለማስላት ዘዴ ዓላማ ሲባል በውሉ ይገኛል ተብሎ የተገመተው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በኤርግጠኛነት ከተገኘው ግብር ካሚኩተለበት ገቢ በልጦ ሲገኝ እና፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የርዕሰ መሳፍንት ጽ/ቤት
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(ሀ) መሠረት በብልጫ የታየው ገንዘብ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተሰልቶ ከተደረሰበት ውሉ በተጠናቀቀበት የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢና ወጪው መካከል ካለው ልዩነት በልጦ ሲገኝ፣

፮). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም **"ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ውል"** ማለት ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንሰቶ በ፲፪ ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዓመት ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው።

ምዕራፍ ሦስት

ድርጅቶች

፴፩. <u>አንድን ድርጅት በመቆጣጠር ረገድ የሚደረግ ለውጥ</u>

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ድርጅት "የኪሳራ ዓመት" ተብሎ በሚጠቀሰው የግብር ዓመት የደረሰበት ኪሳራ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ ወይም አንቀጽ ፶፯ መሠረት "የመሸጋገሪያ ዓመት" ተብሎ ወደ ሚጠቀሰው የሚቀጥለው ዓመት ሊያሸጋግር የሚችለው በኪሳራው ዓመት፣ በማሸጋገሪያው ዓመት እና በማናቸውም ጣልቃገብ ዓመታት የኩባንያውን ከ50% በላይ የሆነውን የባለቤትነት ድርሻ የያዘው ሰው ተመሳሳይ ሰው የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የኪሳራ መሸጋገርን መከልከል የማይቻለው፡-

ሀ/ በኪሳራው ዓመት፣ በማሸጋገሪያው ዓመት እና በሁሉም ጣልቃገብ የግብር ዓመታት ድርጅቱ አንድ ዓይነት የንግድ ሥራ የሠራ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ የድርጅቱ ዋና ባለቤትነት ከተለወጠም በኋላ የደረሰው ኪሣራ ባወጪነት ተቀናሽ ተደርጐ እስከሚጠናቀቅ ድረስ፣ ድርጅቱ በአዲስ የንግድ ሥራ ያልተሠማራ እና ድርጅቱ ወይም የድርጅቱ አባላት በአዲስ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩበት ዋነኛ ዓላማ የደረሰው ኪሣራ በአዲሱ የንግድ ሥራ ከተገኘው ገቢ ላይ ተቀናሽ እንዲሆን ቢማድረግ በድርጅቱ ሊከፈል የሚገባውን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ለማሳነስ ያልሆነ እንደሆነ ነው።

፴፩. የኩባንያ እንደገና መደራጀት

፴፩/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ "አስተላላፊ" ተብሎ የሚጠራ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ "የሚተላለፍለት" ተብሎ ለሚጠቀስ ሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ እንደገና ከመደራጀት ጋር ተያይዞ የንግድ ሥራ ሀብት ያስተላለፈለት እንደሆነ፤

ሀ/ ማስተላለፉ የንግድ ሥራ ሀብትን እንደመሸጥ፣ መለወጥ ወይም መስጠት ተደርጎ አይወሰድም፤

ለ/ የንግድ ሥራ ሀብቱ የተላለፈለት ኩባንያም የንግድ ሥራ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ አስተላለፊው የንግድ ሥራ ሀብቱን ለማግኘት ካወጣው ወጪ ጋር እኩል የሆነ ወጪ በማውጣት የንግድ ሥራ ሀብቱን እንዳገኘው ተደርጎ ይወሰዳል።

ሐ/ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው በተላለፈለት ሀብት ለውጥ አክሲዮን የሰጠ እንደሆነ ለአክሲዮኖቹ የተደረገው ወጪ፣ የተላለፈው ሀብት ማስተላለፍ በሚከናወንበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የንግድ ሥራ ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የሆነ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለንግዱ ሥራ ሀብት የተደረገው ወጪ በሚል የተጠቀሰው የሀብቱ መተላለፍ በሚደረግበት ጊዜ ያለውን የንግድ ሥራ ሀብቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚመለከት ይሆናል።

፫). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "እንደገና መደራጀት" ማለት

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች መዋሃድ፤

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነውን ኩባንያ ድምጽ የሚያሰጥ የአክሲዮን ዋጋ ሃምሳ በመቶ (፶%) ወይም የሌሎች ጠቅላላ የአክሲዮኖች ዋጋ ሃምሳ በመቶ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ አባል የሚሆን ድርጅት በሚያገኘው አክሲዮን ለውጥ ብቻ የተሸጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ እንደሆነ፣

ሐ/ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ ውስጥ አባል ለሆነ ኩባንያ በአክሲዮን ድርሻ ክፍያ ረገድ ልዩ መብት በሚያሰጥና የድምጽ ተሳትፎ ብቻ በሚያስገኝ አኳኋን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ እና የእንደገና መደራጀቱ አባል ከሆነ ኩባንያ ሃብት ውስጥ ሃምሳ በመቶ ወይም ከዚህ በላይ ሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የተሰጠ ወይም የተላለፈ እንደሆነ፣

መ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ ኩባንያዎች ሲከፋፈል፤ ወይም

ሠ/ አንድ የንግድ ሥራ ድርጅት የተቀጽላዎቹን ካፒታል፣ የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ ሲያከፋፍል ነው።

፱). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን የተደረገው ውሀኖት፣ በባለቤትነት መያዝ፣ መጠቅለል፣ መከፋፈል ወይም የተቀጽላዎቹን ካፒታል የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ የማስተላለፍ ተግባር ዋንኛ ዓላማ ከታክስ ለመሸሽ ያለመሆኑን ሲያምንበት ነው።

ምዕራፍ አራት

የማዕድን ሥራዎች

፴፯. ትርጓሜ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በማዕድን ሥራዎች አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ ምዕራፍ ሥር፦

፩). "ሥራ ተቋራጭ" ማለት ከመንግሥት ጋር የማዕድን ማውጣት መብት ያደረገ ማንኛውም ሰው ነው።

፪) "መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነት" ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ተፈጻሚ የሚሆንበት ስምምነት ነው።

፫). "የማልሚያ ወጭ" ማለት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የሚወጣን ወጪን ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በስራ ተቋራጩ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት የሚወጣ የካፒታል ወጪ ሲሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል።

ሀ/ የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን በማናቸውም ጊዜ የሚወጣ ወጪ፦

፩."የፍለጋ ወጪ" ለሚለው ሀረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭(ሀ)(፩) በተሰጠው ትርጉም የተመለከተውን ጥቅም ሳይጨምር፣ በማዕድን ማውጣት ሥራ ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፣ ወይም

፱."**የፍለጋ ወጪ**" ለሚለው ሀረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ (ሀ)(፱) በተሰጠው ትርጉም የተመለከተውን ሳይጨምር የማዕድን ማውጣት ስራ መረጃ ለማግኘት የወጣ ወጪ፤

ለ/ ከማዕድን ማውጣት መብት ጋር በተያያዘ ለማህበራዊ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ የሚወጣ ወጪ፣

፲). **"ፋልማት ሥራምች"** ማለት ለማዕድን ማውጣት ሥራ ሲሆን በማዕድን ማውጫት ሥራ ፈቃድ የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው።

፲፩). **"የፍለጋ ወጭ"** ማለት ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች የሚወጣውን ወጪ ሳይጨምር ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በስራ ተቋራጩ የምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚወጣ ወጭ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

ሀ/ የሚከተሉትን ለማግኘት የወጣ ወጪ

፩. ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋን መብት የሚመለከት ጥቅም ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም

፪ ከመንግሥት ወይም መብትን ከሚያስተላልፍ ስምምነት የፍለጋ መረጃን ለማግኘት የሚወጣ ወጪ፤ ወይም

ለ/ ከማዕድን ፍለጋ ሥራ ጋር ተያይዞ ለማህበራዊ መሠረተ-ልማት ግንባታ የሚወጣ ወጪ፤

፲፪)."**የፍለጋ መረጃ**" ማለት በማዕድን ፍለጋ መብት ውስጥ የተካተቱ ማዕድናትን ለማግኘት ለሚደረግ ፍለጋ የሚያገለግል መረጃ ነው።

፲፫). **"የፍለጋ ሥራ"** ማለት ለማዕድን ፍለጋ ሲሆን በማዕድን ፍለጋ መብት ውስጥ የተፈቀደ ሥራ ነው፡

፲፬). **"የፍለጋ መብት"** ማለት በማዕድን አዋጅ መሠረት በመንግሥት የተፈቀደ የማዕድን ፍለጋ መብት መሠረት የተሰጠ የፍለጋ ፈቃድ ነው።

፲፭). **"ፈቃድ የተሰጠበት አካባቢ"** ማለት የማዕድን ማውጣት ፈቃድ የተሰጠበት አካባቢ ነው።

፲፮). **"ፈቃድ የተሰጠው ሰው"** ማለት ማዕድን የማውጣት መብት የተሰጠው ሰው ነው።

ሠ) **"የማዕድን ፍለጋ መብት"** ማለት በማዕድን አዋጅ መሠረት የተሰጠ የቅኝት፣ የፍለጋ፣ ወይም ፈቃድን ይዞ የመቆየት መብት ነው።

ረ). **"የማዕድን መረጃ"** ማለት ከማዕድን ሥራዎች ጋር የተያያዘ መረጃ ነው።

ሰ). **"የማዕድን ሥራዎች"** ማለት በማዕድን መብት መሠረት የተፈቀዱ ሥራዎች ናቸው።

ሸ). **"የማዕድን መብት"** ማለት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት በመንግሥት የሚሰጥ የቅኝት፣ የምርመራ፣ ፈቃድን ይዞ የመቆየት ወይም የማዕድን ማምረት ፈቃድ ነው።

ቀ). **"የማህበራዊ መሠረተ-ልማት ወጪ"** ማለት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ በማዕድን ሥራ መብት ባለበት ግዴታ መሠረት የህዝብ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታልን፣ መንገድን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማህበራዊ መሠረተ-ልማት ለመገንባት የሚያወጣው የካፒታል ወጪ ወይም ለህብረተሰብ ልማት ፈንድ የሚያደርገው መዋጮ ነው።

በ). **"ንዑስ-ሥራ ተቋራጭ"** ማለት በተቀጣሪነት አገልግሎት የሚሰጥን ሰው ሳይጨምር፣ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ከማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሰው ነው።

ተ). **"ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት በሞተር ኃይል በማይንቀሳቀስ መሣሪያ በመታገዝ አበዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን ሆኖ አግባብ ባለው ህግ በተቋቋመ የማዕደን የህበረት ሥራ ማህበር ወይም በአንድ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ የሚካሄድ የወርቅ፣ የፕላቲኒየምና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት ፣የብረት፣የጨው ፣የኮንስትራክሽን ማእድናት፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉት ማዕድናት የማምረት ሥራ ነው።

፴፮. ፈቃድ በተሰጠው ሰው እና ሥራ ተቋራጭ ላይ ግብር ስለመጣል

፩). በዚህ ምዕራፍ የተቀመጡት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህ አንቀጽ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፪). ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ የሚጣለውን ግብር በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ እና በአዋጁ ሌሎች ክፍሎች በተደነገገው መካከል አለመጣጣም የተፈጠረ እንደሆነ ይህ ምዕራፍ ተፈጻሚ ይሆናል።

፫). በክልሉ ውስጥ በማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም ሥራ ተቋራጭ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ እንደሚከተለው ይሆናል።

ሀ) ባህላዊ የማእድን ማምረት ሥራ----------12 %(አሥራ ሁለት በመቶ)

ሰ) የልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ--15% (አሥራ አምስት በመቶ)

ሐ) የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ----18% (አሥራ ስምንት በመቶ)

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ከተደነገገው ውጭ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ነው።

፭). ፈቃድ የተሰጠው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ንዑስ -ሥራ ተቋራጭ ከሚፈጽመው ማንኛውም ክፍያ ላይ 10% ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት።

፮) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚከፈለው የግብር መጠን የሚሰላው የሞቢላይዜሽን እና የዲሞቢላይዜሽን ወጪዎች ተቀናሽ ተደርጎ ነው።

፯). ከኮንስትራክሽን፣ ከኢንዱስትሪ እና ከባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ከሚገኝ ገቢ የሚከፈል ግብርን በሚመለከት የክልሉ መስተዳድር ም/ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሚወሰን ይሆናል።

፴፱. በማዕድን ሥራዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች ገደብ

፩). ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃድ ክልል ውስጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ ለመሥራት የሚያወጣው ወጪ በተቀናሽነት የሚያዝለት ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ በግብር ዓመቱ ካገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ብቻ ነው።

፪). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ በግብር ዓመቱ የማዕድን ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ይህ ኪሳራ ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ተሸጋግሮ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ በመስራት ከሚያገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።

፫). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሙሉ በሙሉ መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ያልተቀነሰውን ኪሳራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ማሸጋገር እና የተካካሰውን መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው መሠረት በዚያው የግብር ዓመት ከተገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ በመቀነስ ኪሳራው ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ተደርጎ እስከሚያልቅ ድረስ ማሸጋገር የሚችል ሲሆን፣ነገር ግን ፈቃድ የተሰጠው ሰው የደረሰበትን ኪሳራ ኪሳራው ከተከሰተበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠሩ አሥር የግብር ዓመታት በላይ ማሸጋገር አይቻልም።

፬). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር በተያያዘ ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ውስጥ ኪሳራ ደረሰበት የሚባለው በፈቃድ ክልል ውስጥ ከሚያከናውነው የማዕድን ማውጣት ሥራ ጋር

ብተያያዘ በግብር ዓመቱ በተቀናሽነት የሚያዝለት ወጪ በዚሁ ግብር ዓመት በዚሁ ክልል የማዕድን ማውጣት ሥራ በመሥራት ካገኘው የንግድ ሥራ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ነው።

፵. የፍለጋ ወጭ

፩). ለዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ አፈጻፀም፣ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም በሥራ ተቋራጩ ለፍለጋ የሚወጡ ወጪዎች የአገልግሎት ዘመናቸው አንድ ዓመት የሆኑ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ተደርገው ይወሰዳሉ።

፪). ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ለፍለጋ ሥራ የሆነ ዋጋው የሚቀንስ የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ምጣኔው ፻% (መቶ በመቶ) ይሆናል።

፵፩. የማልሚያ ወጭ

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ አፈጻፀም ሲባል ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የማልሚያ ወጪ ለአራት ዓመታት ያህል የሚያገለግል ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ ለንግድ የሚውል ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት የማልሚያ ወጪ ያወጣ እንደሆነ፣ ይህ ወጪ ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት ጊዜ እንደወጣ ወጪ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

፫). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ ለንግድ ሥራ የሚሆን ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ለማልሚያ ሥራዎች አገልግሎት የሚውል ዋጋው ሊቀንስ የሚችል ሀብት የገዛ ወይም የገነባ እንደሆነ ይህ ሀብት ለንግድ ሥራ የሚሆን ምርት በተጀመረበት ጊዜ እንደተገዛ ወይም እንደተገነባ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የሚፈቀደው የማልሚያ ወጪ ተቀናሽ መጠን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በእርጅና ምክንያት ዋጋው ለሚቀንስ የንግድ ሥራ ሀብት በግብር ዓመቱ የሚደረገው የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፦

$$ሀ \times {}^{ሳ}/_{ሐ}$$

ሀ - የወጪው መጠን ወይም ለሀብቱ የተደረገ ወጭ፣

ለ - ለንግድ ማምረት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ለንግድ ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት የመጨረሻ ቀን መካከል ያሉት ቀናት፣

ሐ - ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት በተጀመረበት የግብር ዓመት ያሉት ቀናት ብዛት፣

፫). መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነትን ሳይጨምር፣ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከማዕድን ሥራ መብት ውስጥ አንድ ጥቅም ያስተላለፈ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ መብቱን በማስተላለፍ የሚያገኘው ጥቅም ተደርጎ የሚወሰደው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ተቀናሽ የተደረገለትን ወይም በማናቸውም መንገድ ያልመለሰውን ሂሣብ ሳይጨምር ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ ያወጣው የማልማያ ወጪ ከተቀነሰ በኋላ ነው።

፬). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም"ለንግድ የሚሆን ምርት ማምረት መጀመር" ማለት የማዕድን ቢሮው በሚወሰነው መሠረት፣ከ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከፍተኛ ምርት ማምረት የተቻለባቸውን ፸፯ ቀናት ካሉት ፴ ቀናት ውስጥ የመጀመሪያው ቀን ነው።

፵፪. የመልሶ ማቋቋሚያ ወጪ

፩). በተፈቀደ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ ከማዕድን ሥራዎች ጋር ተያይዞ በግብር ዓመቱ ለመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ የሚያደርገው መዋጮ መዋጮው በተደረገበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዛል።

፪). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የማዕድን ሥራን በሚመለከት በጸደቀ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት ለሚሰራው ሥራ የሚያወጣው ወጪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ያልተከፈለው እንደሆነ ወጪው በወጣበት የግብር ዓመት በተቀናሽነት ይያዝለታል።

፫). በመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ውስጥ የሚጠራቀም ገንዘብ ወይም በመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ መሠረት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ከማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ የሚደረግ ገንዘብ ከገቢ ግብር ነፃ ነው

፱). ከመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ወጪ ሆኖ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ ተመላሽ የተደረገ ገንዘብ ተመላሽ በተደረገበት የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የንግድ ሥራ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል።

፲). የመልሶ ማቋቋሚያ ሥራ በሚጠናቀቅት ጊዜ ፈቃድ በተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጭ የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ውስጥ ትርፍ ገንዘብ በሚኖርበት ጊዜ ይህ ገንዘብ የመልሶ ማቋቋሙ ስራ በተጠናቀቀበት የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የንግድ ሥራ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል።

፲፩). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ) "የፀደቀ የመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ" ማለት በማዕድን መብት የሚወሰኑትን ግዴታዎች ጨምሮ የማዕድን ቢሮ የፀደቀ የማዕድን ማውጫ ቦታ መልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ ነው።

ለ) "መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ" ማለት በማዕድን መብት የተሸፈነውን ክልል ለማስተካከል ለወደፊት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን በማዕድን መብት መሠረት መቀመጥ የሚገባው እና የማዕድን ቢሮ እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በጋራ የሚያስተዳድሩት ገንዘብ ነው።

፵፫. ስለኢንቨስትመንት ተቀናሽ

፩). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጩ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በተፈቀዱ ሌሎች የልማት መስኮች ወጪ ሆኖ ኢንቨስት ለማደረግ የኢንቨስትመንት ወጪ ከእያንዳንዱ የግብር ዓመት ጠቅላላ ገቢው ላይ እስከ ፭% (አምስት በመቶ) መቀነስ ይችላል።

፪). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በአንድ የግብር ዓመት ተቀናሽ ያደረገውን የገንዘብ መጠን ተቀናሽ ከተደረገበት የግብር ዓመት ቀጥሎ እስካለው የግብር ዓመት መጨረሻ ድረስ ኢንቨስት ካላደረገ በዚሁ የግብር ዓመት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጭ ጠቅላላ ገቢው ላይ ይደመራል።

፵፬. መብትን ስለማስተላለፍ

፩). መብትን ማስተላለፍ ተፈፃሚ የሚሆኑት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

ሀ/ "ለስተላላፊ" ተብሎ የሚጠቀሰው ባለፈቃድ ወይም ሥራ ተቋራጭ በማዕድን ማውጣት መብት ያገኘውን የተወሰነ መብት "መብት የተላለፈለት" ተብሎ

የሚጠቀሰው ሌላ ሰው ለማስተላለፍ "የማስተላለፍ ስምምነት" ተብሎ የሚጠቀስ ስምምነት ያደረገ እንደሆነ፤

ለ/ መብቱ የተላለፈለት ሰው ከመብት አስተላላፊው በሙሉ ወይም በከፊል ለተላለፈለት መብት የሚከፍለው ዋጋ መብት የተላለፈለት ሰው ሊከፍል የተስማማበትን ወጪ ወይም መብት አስተላላፊው ካስቀረው የተወሰነ መብት የሚመነጩ የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም ግዴታዎች መብት አስተላላፊውን ተክቶ ለመወጣት የሚገባውን ግዴታም ይጨምራል።

፪). መብትን ማስተላለፍ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣

ሀ/ መብት አስተላላፊው ካስቀረው መብት ጋር በተያያዘ መብት የተላለፈለት ሰው የሚያከናውነው ስራ ዋጋ በሚከተሉት ውስጥ አይካተትም፤

፩. መብት አስተላላፊው ለተላለፈው መብት በተቀበለው ዋጋ፣ ወይም

፪. በመብት አስተላላፊውን የንግድ ሥራ ገቢ፣ እና

ለ/ መብት አስተላላፊው ለተላለፈው መብት በተቀበለው ወይም በሚቀበለው ገንዘብ ላይ የሚከተሉት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

፩. መብት አስተላላፊው ከተላለፈው መብት ጋር በተያያዘ ላወጣው ወጪ ያገኘው ተቀናሽ ተመላሽ በመደረጉ ምክንያት በተቀበለው የገንዘብ መጠን ላይ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፣

፪. መብት አስተላላፊው ከተቀበለው ገንዘብ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆንበት ተቀናሽ ወጪ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን የተላለፈው መብት ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

፵፭. የማዕድን መብትን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለማስተላለፍ

፩). ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ የነበረው ዋና የባለቤትነት መብት ከ፶% (ከአስር በመቶ) በላይ የተለወጠ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ሥራ ተቋራጩ ይህንኑ ለውጥ ወዲያውኑ ለገቢዎች ቢሮ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

፫/. በአንድ ድርጅት ውስጥ የአባልነት መብቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስተላልፈው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተጠቀሰውን ማስታወቂያ መስጠት ያለበት ሰው የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው ወኪል እንደሆኑ ተቆጥሮ ከማስተላለፉ ጋር ተያይዞ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የሥራ ተቋራጩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነውን ሰው በመወከል የከፈሉት ማንኛውም ግብር በዚህ አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነው ሰው ላይ ከሚፈለገው የታክስ ዕዳ ጋር ይካካሳል።

፬). ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለው የአባልነት ጥቅም እንደ ንግድ ሥራ ሀብት ተደርጎ ይወሰዳል።

ምዕራፍ አምስት

ዓለም ዐቀፍ ግብር

፵፯. በውጭ ሀገር የተከፈለን የንግድ ሥራ ግብር ስለማካካስ

፩). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፍልበት ገቢ ያለው እንደሆነ እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር ከፍሎበት ከሆነ ግብር ከፋዩ ባውጭ ሀገር የከፈለው ግብር "በውጭ ሀገር ለተከፈለ ግብር የሚደረግ ማካካሻ" ተብሎ የሚካካስለት ከሚከተሉት ከአነስተኛው መጠን ጋር እኩል የሚሆነው የገንዘብ መጠን ነው።

ሀ/ በውጭ ሀገር የተከፈለው የገቢ ግብር፤ ወይም

ለ/ በውጭ ሀገር በተገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተከፋይ የሚሆነው የንግድ ገቢ ግብር፣

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) የተመለከተው የንግድ ገቢ ግብር የሚሰላው በንግመቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነው ግብር ከፋይ ላይ ተፈፃሚ የሚደረገውን አማካይ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔ ግብር ከፋዩ ባገኘው የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ተፈፃሚ በማድረግ ነው።

፫). በዚህ አንቀጽ መሠረት በውጭ ሀገር የተከፈለ ግብር ሊካካስ የሚችለው

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር ባገኘው ገቢ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ገቢው ከተገኘበት የግብር ዓመት በኋላ ባሉት ሁለት ዓመታት ወይም ደግሞ ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የከፈለ እንደሆነ፤ እና

ለ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው ለከፈለው ግብር በውጭ አገር የታክስ ባለሥልጣን የተሰጠ ደረሰኝ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው።

፬). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በግብር ዓመቱ መክፈል የሚኖርበትን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ሲያሰላ፣ ማንኛውንም የግብር ማካካሻ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በውጭ ሀገር ለተከፈለ ግብር የተፈቀደውን ማካካሻ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

፭). በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው በውጭ ሀገር የከፈለው ግብር በዚያው የግብር ዓመት ሙሉ በሙሉ የማይካካስ የሆነ እንደሆነ ሳይካካስ የቀረው ግብር ተመላሽ ሊደረግ ወይም ወደቀደመው የግብር ዓመት ሊመለስ ወይም ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ሊሸጋገር አይችልም።

፮). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፣

ሀ) **"አማካኝ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ሰው የግብር ዓመቱ ግብር በሚከፍልበት ገቢ ላይ ተግባራዊ የሚሆነው ምጣኔ ነው።

ለ) **"የውጭ ሀገር ገቢ ግብር"** ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር አካባቢያዊ መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ታክስን፣ ወይም ደግሞ ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም።

ሐ) **"የተጣራ የውጭ ሀገር ገቢ"** ማለት በአንድ የግብር ዓመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት በዚህ ሰንጠረዥ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር ገቢ ላይ ለግብር ከፋዩ በዓመቱ በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈቀደው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው።

፮. የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት ሲባል ብቻ ወጪ የተደረገ እና

፪. በውጭ ሀገር የሚገኝ ገቢ እራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚመደብ በመሆኑ የውጭ ሀገር ገቢውን ለማግኘት በወጣው መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 73 መሠረት የተከፋፈለ ሲሆን፣

፵፯. የውጭ ሀገር የንግድ ሥራ ኪሳራዎች

፩). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢን ለማግኘት ያወጣው ወጭ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ የሚደረግለት በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ ብቻ ነው።

፪). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት በውጭ ሀገር ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዘመን ቀጥሎ ላለው የግብር ዘመን የሚሸጋገር ሆኖ ይህም ኪሳራ በተሸጋገረበት የግብር ዓመት ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር ካገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል።

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ግብር ከፋይ ኪሳራውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል መቀነስ ያልቻለ እንደሆነ ኪሳራው በሙሉ ተቀንሶ እስኪሚያልቅ ድረስ ወደ ሚቀጥሉት የግብር ዓመታት ተሸጋግሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ተቀናሽ ይደረጋል፡ ፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ ኪሳራው ከደረሰበት የግብር ዓመት በኋላ ካሉት አምስት የግብር ዓመታት በላይ ኪሳራውን ለማሸጋገር አይችልም።

፬) ግብር ከፋዩ የውጭ ሀገር ኪሳራ ያስተናገደባቸው ሁለት ዓመታት የኖሩ እንደሆነ እና አያንዳንዱ ኪሳራ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተሸጋገረ እንደሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ተጨማሪ ኪሳራዎችን ለማሸጋገር አይፈቀድለትም።

፭). አንድ ግብር ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ ኣንቀጽ ፪ እና ፫ የተመለከቱትን የውጭ ሃገር ኪሳራዎች ሊያሸጋግር የሚችልበት ዝርዝር የአፈፃፀም ሥርዓት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፮). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም በአንድ የግብር አመት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን ግብር ከፋይ በሚመለከት፣ "በውጭ ሀገር የደረሰ ኪሳራ" ማለት ግብር ከፋዩ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን የውጭ ሀገር ገቢ ለማግኘት ያወጣቸው ወጪዎች መጠን ከጠቅላላው የውጭ ሀገር ገቢ በልጦ ሲገኝ ነው።

፰. ለኩባንያ ካፒታል የሚወሰድ ብድር

የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ድርጅቶችን ሳይጨምር በውጭ አገር ባለአክሲዩኖች ቁጥጥር ስር ያለና በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ የግብር ዓመቱ አማካኝ ዕዳ ከአማካኝ የካፒታል መዋጮ ከ፪ ለ ፩ የበለጠ እንደሆነ ኩባንያው ለወለድ ክፍያ ያወጣው ወጪ ከዚህ በታች በተመለከተው ስሌት መሠረት በተቀናሽ እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

$$ሀ \times \frac{ሰ}{ሐ}$$

በዚህ ስሌት

ሀ/ ኩባንያው ባግብር ዓመቱ ተቀናሽ እንዲደረግለት የሚጠይቀው የወለድ ወጪ፣

ለ/ ኩባንያው ካተፈቀደው መጠን በላይ የወሰደው ብድር እና

ሐ/ ኩባንያው በግብር ዓመቱ ያለበት አማካኝ ዕዳ፣

፪). በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ አማካኝ ዕዳ እና አማካኝ የካፒታል መዋጮ በግብር ዓመቱ ከ፪ ለ ፩ የበለጠ እንደሆነ እና የኩባንያው የግብር ዓመቱ አማካይ ዕዳ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ከተወሰደው ዕዳ የማይበልጥ ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፫). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ኩባንያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሀ/ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ሆኖ ይቆጠራል፣

ለ/ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝ ዕዳ እና አማካኝ የካፒታል መዋጮ የሚከተለውን መሠረት በማድረግ ይሰላል፡፡

፩. በቋሚነት ለሚሠራው ድርጅት የዋለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ የወሰደው ብድር፣

፪. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ ለሥራው ማንቀሳቀሻ የመደበውና በቋሚነት በሚሠራው ድርጅት አማካኝነት ሥራ ላይ የዋለው የካፒታል መዋጮ፣

፬). . ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ/."**ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች የተወሰደ ዕዳ**" ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በማመልከት፣ አንድ የፋይናንስ ተቋም ኩባንያው የሚገኝበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት

ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት አኳኋን ሊያባድረው የሚችለው ገንዘብ ነው።

ሰ/. **"አማካኝ ዕዳ"** ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት በግብር ዓመቱ ውስጥ የወሰደው በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን ዕዳ ነው።

ሀ/ገ

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

፩. በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ኩባንያው የሚፈለግበት ጠቅላላ የዕዳ መጠን ነው።

ሐ/. **"አማካኝ የካፒታል መዋጮ"** ማለት፣ በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተከፈለ በሚከተለው ቀመር ስሌቱ የሚከናወን የካፒታል መዋጮ ነው።

ሀ/ገ

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

፩ በሚቀጥለው የግብር ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ለኩባንያው የተደረገ ጠቅላላ የካፒታል መዋጮ መጠን ነው።

መ/. **"ዕዳ"** ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር የሚገኝን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በሚወሰነው መሠረት ወለድ የሚከፈልበት የኩባንያው ዕዳ የመክፈል ግዴታ ነው።

ሠ/. **"ዕዳ የመክፈል ግዴታ"** ማለት ከቃል ኪዳን ሰነድ፣ ከሀዋላ፣ እና ከቦንድ የሚመጣን ግዴታ ጨምሮ ለሌላ ሶው ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም።

፩. ተከፋይ ሂሳቦችን፣ ወይም

፪. ወለድ የመክፈል ግዴታን የማያስከትል ማናቸውንም ገንዘብ መልሶ የመክፈል ግዴታ፣

ረ/. **"የካፒታል መዋጮ "** ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ የወለድ ክፍያን የማይጨምር ዕዳን መልሶ የመክፈልን ግዴታ የሚያስከትል ብድርን ጨምሮ በሂሳብ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት በግብር ዓመቱ ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛው የኩባንያው የካፒታል መዋጮ ነው።

ሰ/. **"በብልጫ የታየ ዕዳ"** ማለት በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለን በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ በሚመለከት፣ በግብር ዓመቱ ውስጥ ኩባንያው ያለበት አማካኝ ዕዳ በ2 ለ 1 ቀመር መሠረት ከተፈቀደለት ከፍተኛው አማካኝ ዕዳ በላይ የሆነው የገንዘብ መጠን ነው።

ሸ/. **"በውጭ አገር ባለአክሲዮኖች ቁጥጥር ስር ያለ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ"** ማለት ኩባንያው የአባልነት ጥቅም መካከል ከ፶% በላይ የሚሆነው በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆኑ ሰዎች ግንኙነት ካለው ወይም ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን የተያዘ ኩባንያ ነው።

ምዕራፍ ስድስት

በግምት ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥራ ግብር

፵፱. <u>የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል</u>

፩). በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ የታክስ ህግ የተደነገገው ቢኖርም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዩች ግብር የሚከፍሉት በጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ ይሆናል።

፪). ግብሩ የሚጣለው እና ሶሚከፈለው በግብር አመቱ ውስጥ ከእቃ እና ከአገልግሎት ሽያጭ በሰበሰቡት ጠቅላላ የሽያጭ ገበ. ላይ ነው።

፫). በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው ግብር ማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፦

ንዑስ አንቀጽ "ለ" ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት በየክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር አሰፋፈል ዘዴ ነው፡

፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ዓመታዊ ሽያጫቸው ፪ (ሁለት) ሚሊዮን በታች ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ሥር በተመለከቱት መጣኔዎች መሠረት የሚከፍሉ ይሆናል።

ክፍል አምስት

ሠንጠረዥ "መ" - ሌሎች ገቢዎች

፶. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰዎች ገቢ

፩). በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ ወለድ፣ ሮያሊቲ፣ ከሥራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ከኢትዮጵያ ውስጥ ያገኘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከው ምጣኔ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፤

፪). በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰው ግብር የሚከፍልበት ምጣኔ ፦

ሀ) ጠቅላላ ክፍያ ላይ ለመድን በሚከፈል አረቦን ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ) እና ሮያሊቲ ፲% (አስር በመቶ)

ለ) በትርፍ ድርሻ በጠቅላላ ገቢ ላይ ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ)፤

ሐ) በወለድ በጠቅላላ ገቢ ላይ ፲% (አሥር በመቶ)፤

መ) ከሥራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ላይ ከጠቅላላ ገቢው ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ) ፤

፫). የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ፣ የሮያሊቲ፣ የስራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ገቢ የተገኘው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያከናውነው ሥራ የሆነ እንደሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተፈፃሚ አይሆንም። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እነዚህ ገቢዎች እንደሁኔታው በሰንጠረዥ "ሐ" ወይም "መ" መሠረት ግብር ይከፈልባቸዋል።

፬). ከኮንስትራክሽን ፣ከማዕድን ፣ ከደን እና ደን ውጤቶች ከተሰማራ ግብር ከፋይ የማስከፈያ መጣኔ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል።

፶፩. የዲጂታል አገልግሎት ግብር

፩). በክልሉ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎትን በማቅረብ ገቢ የሚያገኝ ነዋሪ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ገቢ ግብር ይከፈልበታል።

ግብር የሚከፈልበት አማዊ ጠቅላላ ገቢ		መጣኔ
ከብር	አስከ ብር	
0	100,000	2%
100,001	500,000	3%
500,001	1,000,000	5%
1,000,001	1,500,000	7%
1,500,001	2,000,000 በታች	9%

፬).የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለሚከተሉት ተፈጻሚ አይሆንም፦

ሀ) የሚከተሉትን ጨምሮ የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች፦

(፩) ለሂሳብ አያያዝ ሙያ፤

(፪) ለኦዲት ሙያ

(፫) ለአርኪቴክቶች፤

(፬) ለአማካሪዎች፤

(፭) ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፤

(፮) ለመሃንዲሶች፤

(፯) ለፋይናንስ፣ ለኦኮኖሚ እና ለኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፤

(፰) ለጤና ባለሙያዎች፤

(፱) ለህግ ባለሙያዎች፤

(፲) የአስተዳደር፣

(፲፩) የቅየሳ፣

(፲፪) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፤

(፲፫) ማህበራዊ ጉዳይ፣ ወይም በሌላ ተመሳሳይ መስክ የሚሰጥ የሙያ አገልግሎት

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች፤ እና

ሐ) የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል ለመረጡ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች፤

፭). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ቡተዘረዘሩት ሙያዎች የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በዚህ አዋጅ ለደረጃ "ሀ" የሚጠየቀውን የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚከፈለው ግብር ከ፭% (አምስት በመቶ) የማይበልጥ ሲሆን የማስከፈያው መጣኔ፣ የአከፋፈሉ ሁኔታ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፶፪. እንዲተካ በተጠየቀ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ እና ሮያልቲ ላይ ስለሚከፈል ግብር

፩). ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል።

ሀ/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ሳይሆን ለራሱ የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ (ሊዝ) አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፣

ለ/ የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የመሣሪያ ኪራይ (ሊዝ) አገልግሎት የተሰጠው ("አገልግሎት ተቀባይ" ተብሎ የሚጠቀሰው) ሰው፣

፩/ ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የሚሰጠውን አገልግሎት ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ፣ ወይም

፪/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እና በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያከናውን ከሆነ፣

ሐ/ ከአቅርቦቱ ወይም ከሊዙ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያ የተከፈለው ከአገልግሎት ተቀባዩ ጋር ግንኙነት ባለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሆነ እንደሆነ

መ/ ግንኙነት ያላው ሰው የቴክኒክ አገልግሎት ወይም የሮያሊቲ ክፍያውን ካአገልግሎቱ ተቀባዩ የጠየቀ እንደሆነ፣

፪). ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ግንኙነት ያለው ሰው ለአገልግሎቱ ተቀባይ የቴክኒክ አገልግሎቱን ወይም የመሣሪያውን ሊዝ አገልግሎት እንደሰጠ ተቆጥሮ እንዲሁም እንዲተካ የተጠየቀው ገንዘብ ለቴክኒክ አገልግሎቱ ወይም ለመሣሪያው ሊዝ የተከፈለ ክፍያ እንደሆነ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

፶፫. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ግብር

፩). በክልል በሚካሄድ የመዝናኛ አገልግሎት ተሳታፊ የሆነ በኢትዮጵያ ወይም በክልል ነዋሪ ያልሆነ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ቡድን ከመዝናኛ አገልግሎት በሚያገኘው ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ)ግብር ይከፍላል።



፪). በቡድን አባልነት የሚገኝን ገቢ ጨምሮ ከመዝናኛ አገልግሎት የሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ አዝናኙ ሳይሆን ሌላ ሰው ሆኖ እንደሆነ ይህ ሰው በሚያገኘው ጠቅላላ ገዚ ላይ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

፫). ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

"የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪ" ስፖርተኛን እና ሙዚቀኛን ይጨምራል

"ቡድን" የስፖርት ክለብን (ቡድንን) ይጨምራል

"የመዝናኛ አገልግሎት" የስፖርት ውድድርን ይጨምራል

፶፬. ሮያሊቲ

፩) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በክልሉ ውስጥ የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ፤

ሀ) በጠቅላላ የሮሊቲ ክፍያ ላይ ፲% (አስር በመቶ)፤ ወይም

ለ) የሮያልቲ ገቢው የተገኘው ከኪነጥበብ ወይም ከባህላዊ ስራ ከሆነ ፭% (አምስት በመቶ)፤ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪). በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በክልሉ ውስጥ የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላ የሮያልቲ ገቢው ላይ 10%(አስር በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።"

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ወይም ያልሆነ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድን ፣ በደን እና ደን ውጤቶች ከተሰማራ ግብር ከፋይ የማስከፈያ መጣኔ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በደንብ ይወሰናል።

፶፭. የትርፍ ድርሻ

፩). በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ የሆነና የትርፍ ድርሻ ያገኘ ሰው በጠቅላላው የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ ፲፭% (አሥራ አምስት በመቶ) የትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪). በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በክልሉ ውስጥ የትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ገቢው ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።"

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም አንድ ድርጅት በክልሉ ውስጥ ላቋቋመው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ወይም የኩባንያዎች ቡድን አባል ለሆነ በክልሉ ውስጥ ነዋሪ ለሆነ ድርጅት የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ያከፋፈለ እንደሆነ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፭ ድንጋጌዎች በድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት ከተከፋፈለው ሃብት ጋር በተያያዘ የሚፈቀድ ወይም ተቀናሽ የሚደረግ ወጪ የሌለ ሲሆን፤ ግብር ከፋዩ የተከፋፈለውን ገንዘብ ማስቀነስ ወይም

ማካካስ ወይም ገንዘቡ በተላለፈበት አመት ይህንን ሂሳብ በግብር አመቱ የግብር ክፋዩ ገቢ ውስጥ ማካተት የለበትም።

፫). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም **"የኩባንያዎች ቡድን"** ማለት አንድ ኩባንያ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች ውስጥ ፶% (ሃምሳ በመቶ) እና ከዚያ በላይ ያሉ አክሲዮኖች ያሉት እንደሆነ ነው።

፶፮. ወለድ

፩)' በክልሉ ነዋሪ የሆነ ሰው የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፲% (አሥር በመቶ) ግብር ይከፍላል።

፪). በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ ፲% (አሥር በመቶ) ግብር ይከፍላል።

፫). በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም አንድ የፋይናንስ ተቋም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ገንዘብ በማስቀመጥ ወይም በሌላ ተያያዥ አገልግሎት የሚያገኘው ወለድ በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ግብር ከፋዩ እቃን ወይም አገልግሎትን በዱቤ በመሸጥ የሚገኘው ወለድ በሰንጠረዥ "ሐ"መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡

፶፯. ሀብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ

፩). በኢትዮጵያ ውስጥ አልፎ አልፎ ንብረት (ማንኛውንም መሬት፣ቤት፣ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት) በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ሰው ከጠቅላላው የኪራይ ገቢ ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) የኪራይ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፱ ወይም ፶፬ መሠረት ዮሮያሊቲ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፶፰. የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም

፩). አንድ ሰው "ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ተብሎ የሚጠቀሰን የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ምጣኔ መሠረት የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚከፈለው ግብር ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው መጣኔ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ይሆናል።

፫). ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተሰው ቀመር ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፦

ግብር የሚከፈልበት ጥቅም = ሐ- (ሀ + ለ)

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፦

ሀ - ሀብቱ የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ

ለ- ያዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% (ሠላሳ በመቶ)

ሐ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ

፬). በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አንድ ሰው በግብር ዓመቱ ውስጥ አንድን ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲያስተላለፍ ኪሳራ የደረሰበት እንደሆነ ኪሣራው በዚያው የግብር ዓመት በተመሳሳይ ምድብ ያለ ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲሸጥ ከሚገኘው ገቢ ጋር አንዲቻቻል ይደረጋል።

ሀ/ ኪሳራው የሚውለው በዚህ አንቀጽ መሠረት የተገኘን ገቢ ለማቻቻል ነው።

ለ/ ያልተቻቻለው ኪሳራ ተቻችሎ እስከሚያልቅ ድረስ በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ያለ ንብረት በሚሸጥበት ጊዜ ለማካካስ እንዲውል ላልተወሰነ ጊዜ ይሸጋገራል።

ሐ/ አንድ ሰው ግንኙነት ላለው ሰው ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ የደረሰው ኪሳራ ዕውቅና አይሰጠውም።

፭). ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የደረሰው ኪሳራ ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ ለሀብቱ የወጣው ወጪ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ የሚበልጠው የገንዘብ መጠን ነው።

፮). የተላለፈው ግብር የሚከፈልበት ሀብት የንግድ ሀብት በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ ተፈጻሚ ይሆናል።

፯). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም **"ግብር የሚከፈልበት ሃብት"** ማለት አክሲዮን፣ ቦንድ እና ቤት ሲሆን፤ ቤትን በሚመለከት ቤቱ ከመተላለፉ በፊት ለሁለት አመታት ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያገለገለ ሀንጻን አይጨምርም።

፰). ድርጅቱ በባለአክሲዮኖቹ ወይም በድርጅቱ ስም የተመዘገቡ ሀብቶች በሚሸጥበት ወቅት የማይንቀሳቀስ ሀብቶችን በማስተላላፍ የሚገኝ ጥቅም ላይ ፲፭% ግብር የሚከፈልበት ይሆናል።

፱). ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ አፈጻጸም ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

፶፱. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚፈጸም ቀጥተኛ ያልሆነ ዝውውር

፩). የማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ታክስ የሚከፈልበት ገቢ፣ ገቢው ከተገኘበት ቀን ቢፈት ባለው የ፫፻፷፭ ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተሳሰሩ ኩባንያዎች አማካኝነት በክልሉ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳስቀስ ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተያያዘውን አክሲዩን ወይም የአባልነት መብት ዋጋ ከ፳ በመቶ (20%) በላይ በመሸጥ የተገኘውን ገቢ ይጨምራል።

፪). ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም ታክስ በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለል ጥቅም ነው የሚባለው፦

ሀ) ጥቅመ ከመገኘቱ በፊት በነበረው የ፫፻፷፭ ተከታታይ ቀን ጊዜ ውስጥ ከተሸጠው አክሲዮን ወይም ሌላ ጥቅም ዋጋ ውስጥ ከ፶% (ሀምሳ በመቶ) ባላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ክልሉ ውስጥ ካለ የማይንቀሳቀስ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተገኘው ጥቅም መሉ በመሉ፤ ወይም

ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ በሚከተለው ቀመር መሰረት ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም፦

ሀxለ/ሐ

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፦

ሀ) የተገኘው ጥቅም የገንዘብ መጠን፤

ለ) በክልሉ ውስጥ ከሚገኘው የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተያያዘ አክሲዮን ወይም ሌላ ጥቅም ዋጋ፤

ሐ) የጥቅመ ጠቅላላ ዋጋ፤

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው በክልሉ ነዋሪ የሆነ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ሰው ያገኘው ወይም ያስተላለፈው ንብረት በክልሉ ውስጥ እንደሆነ እና ጥቅመም የተገኘው ምንጩ የክልሉ ገቢ እንደሆነ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ መሰረት ግብር ይከፈልበታል።

፫). በክልሉ ውስጥ የሚገኘው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተጠቀሰውን የማይንቀሳቀሰው ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ላይ ቀጥተኛ ባለቤትነት ያለው ሪዉ ቬንቸሮኘሪ መንገድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተሳሰሩ ኩባንያዎች አማካኝነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመላከተው ግብይት የተከናወነ እንደሆነ ይህንኑ ግብይት ወዳያውኑ ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጻ (፩) መሰረት የሚያስተላልፈው ሰው የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ውስጥ የሚገኘው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተጠቀሰውን ንብረት የሚያስተላልፈው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው ወክል እንደሆነ ተቆጥሮ ከማሶሉሰሉ ጋር ተያይዞ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፭). በክልሉ ነዋሪ የሆነ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሰረት ግብር የሚከፈልበትን በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወይም ድርጅት ያስተላለፈ ወይም የማስተላለፉን ተግባር ያመቻቸ እንደሆነ ግብሩ በሌላ ሰው ካልተከፈለ እንደወኪል ተቆጥሮ በአዋጁ አንቀጽ ፶፰ የተመለከተውን ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል።

፮). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ንብረት ያስተላለፈ ሰው ወይም ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬ መሰረት ለገቢዎች ቢሮ ያስተለተላለፈው ንብረት የገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።

፯). በዚህ አንቀጽ መሰረት ለባለሥልጣኑ ቢሮ ያስለተላለፈው ንብረት ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን ያልተወጣ ሰው ወይም ድርጅት በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ቅጣት ይጣልበታል።

፰. ንፋስ አመጣሽ ትርፍ

፩). ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከቱ የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ንፋስ አመጣሽ ትርፍ በመመሪያው በተመላከተው የማስከፈያ ልክ ግብር ይከፈልበታል።

፪). ቢሮው ይሚያወጣው መመሪያ፡-

ሀ/ ንፋስ አመጣሽ ትርፍ ነው ሊባል የሚችለው የገቢ መጠን፣

ለ/ በንፋስ አመጣሽ ትርፍ ላይ የተጣለውን ግብር ሊከፍሉ የሚገባቸውን የንግድ ሥራዎች ዓይነት፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ግብር ሥራ ላይ የሚውልበትን ቀን፣

መ/የግብር አወሳሰኑን ዘዴ እና ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆኑ ታሳቢዎችን፣ እንዲወስን ስልጣን ተሰጥቶታል።

፫). ቢሮው የንግድ ሥራ ባህሪያትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች ንፋስ አመጣሽ ትርፍ የሚባለው የገንዘብ መጠን እንዲለያይ ለማድረግ እንዲሁም የተለያየ የግብር ማስከፈያ ልክ ለመወሰን ይችላል።

፬). በዚህ አንቀጽ "ንፋስ አመጣሽ ትርፍ " ማለት ማንኛውም ያለልፋት የሚገኝ፣ ያልተጠበቀ ወይም ሌላ ተደጋግሞ የማይገኝ ትርፍ ነው።

፷፩ ያልተከፋፈለ ትርፍ

፩). ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በአንድ የግብር አመት ግብር ክተከፈለ በኋላ ለአባለቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል።

፪). ለዚህ አንቀጽ ዓላማ **"ያልተከፋፈለ ትርፍ"** ማለት የኩባንያው የሒሳብ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት አስራ ሁለት (፲፪) ወራት ውስጥ ሰባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም የኩባንያውን ካፒታል ለመጨመር ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ ለሚያካሂድ የውጭ አገር ኩባንያ ያልተላከ ትርፍን ያካትታል።

፫). ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ኩባንያ ትርፉን መልሶ ኢንቨስት እንዳደረገ የሚታሰበው፣ የተጣራ ትርፉን የባለአክሲዮኖቹን አክሲዮን እና የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ሲጠቀምበት ነው።

፬). ባለአክሲዮኖች የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ ቃል ለገቡት አክሲዮን መክፈያ በሚያውሉበት ጊዜ ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ፣ አይነትና መጠን ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፷፪. በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ

፩). በክልሉ ውስጥ በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በክልሉ ውስጥ ካለው በቋሚነት ከሚሰራ ድርጅት የሚላክለት ትርፍ ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ትርፉን የግብር አመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ፲፪ (አስራ ሁለት) ወራት ውስጥ ያልላከ ቢሆንም እንደላከ ተቆጥሮ ግብሩን እንዲከፍል ይደረጋል። ሆኖም ይህ ትርፍ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ በድጋሚ የሚከፈል ግብር አይኖርም።

፫). የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚመራው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል።

፷፫. ሌሎች ገቢዎች

በሠንጠረዥ ሀ፣ ለ፣ ሐ እና በዚህ ሠንጠረዥ ሌሎች አንቀጾች መሠረት የገቢ ግብር የማይከፈልበት ማንኛውንም ገቢ ያገኘ ሰው በጠቅላላ ገቢው ላይ ፲፭% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።

፷፬. ከሠንጠረዥ "መ" ጋር የተያያዙ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩). በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የሚጣል ግብር፣

ሀ/ በሌሎች ሠንጠረገሮች ሥር ግብር ለሚከፈልበት ገቢ ወይም

ለ/ ከገቢ ግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፪). በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የሚጣለው ግብር በገቢው ላይ የመጨረሻ ግብር ይሆናል።

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ያገኘው የሮያሊቲ፣ የትርፍ ድርሻ፣ የወለድ ወይም በአንቀጽ ፶፮ የተመለከተውን ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በመሸጥ ያገኘው ገቢ ከውጭ ሀገር የተገኘ እንደሆነ፣ ይህ ሰው በዚህ ሠንጠረዥ ከሚከፈለው ገቢ ላይ በውጭ ሀገር በዚሁ ገቢ ላይ የከፈለው ግብር ከዚሮ በታች ሳይወርድ ተቀናሽ እንዲደረግ ይፈቀድለታል።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ተቀናሽ ያልተደረገን ግብር ለማሸጋገር አይቻልም።

፭). ግብርን ቀንሶ የመያዝ ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ ክፍል አስር መሠረት ግብሩን ቀንሶ ያስቀረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፣ ፶፪፣ ፶፫፣ ፶፬ ፣ ፶፭ ወይም ፶፮ በተመለከተው መሠረት ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር የመክፈል ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል።

ክፍል ስድስት

ሠንጠረዥ "ሠ" - ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ

፷፭. ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ

፩). ለዚህ አዋጅ አፈጻፀም ሲባል የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነጻ ናቸው፡

ሀ/ ቢሮው በዚህ ፊደል ተራ ተራ (፪) ፣ (፫) ፣ (፬) እና (፭) በተመለከቱት ላይ በሚያወጣው መመሪያ የሚያደርገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ለተቀጣሪው የሚሰፈሉ የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው።

፩). ሠራተኛው ሲታመም አሠሪው ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ፣

፪). በሥራ ውል መሠረት ለሠራተኛው የሚከፈል የትራንስፖርት አበል፣

፫). በሥራ ቦታው ወይም በሥራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለሠራተኛው የሚከፈል አበል

፬). ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ውጭ ሥራውን ለማከናወን ሲንቀሳቀስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጭ እና የውሎ አበል

፭). የመጓጓዣ ወጪው በቅጥሩ ውሉ መሠረት የተከፈለ ከሆነ ከሥራ ቦታው ውጪ ተመልምሎ ለተቀጠረ ሠራተኛ ወደ ሥራው ሲመጣ ወይም ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የሚከፈለው የመጓጓዣ ወጪ፣ እንዲሁም የውጭ ሀገር ሠራተኞች ከሀገራቸው ሲመጡና ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የሚከፈል የመጓጓዣ ወጭ፣

፮). የማዕድን ማውጣት፣ የማኑፋክቸሪንግ እና የግብርና ሥራ የሚሠራ ቀጣሪ ለተቀጣሪው በነፃ የሚያቀርበው ምግብና መጠጥ፣

፯) የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ አገር ለሚመድባቸው ሠራተኞች የሚከፈል አበል፣

ለ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የቦርድ አባል ወይም ፀሐፊ እንዲሁም የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ወይም የከተማ አስተዳደሮች በሚያቋቁሟቸው የጥናት ቡድኖች አባል ወይም ፀሐፊ በመሆን የሚከፈል አበል።

ሐ/ ለሠራተኛው ጥቅም ተብሎ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ፲፮% (አሥራ አምስት በመቶ) ባልበለጠ መጠን በየወሩ በቀጣሪው የሚዋጣ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፡፡

መ/ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ እና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ከግብር ነፃ የተደረገ የጡረታ ገቢ፣

ሠ/ የኢትዮጵያ የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ መንግሥታት ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛ ሥራዎቻቸው ጋር በተያያዘ የሚያገኙት ገቢ፤

ረ/ በዓለም ዐቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነጻ የሆነ የገቢ መጠን፣

ሰ/ በኢትዮጵያ መንግሥት በተደረገ ስምምነት (ከዚህ በኋላ "ከግብር ነፃ የማድረግ የሚያስችል አንቀጽ" ተብሎ የሚጠቀስ) መሠረት ማናቸውም ገቢ ከግብር ነፃ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡

፩. ስምምነቱ የተደረገው ለመንግሥት የገንዘብ፣ የቴክኒክ፣ ሰብአዊ ወይም አስተዳደራዊ እርዳታ ለማቅረብ የሆነ እንደሆነ፣

፪. ከግብር ነፃ ማድረግ የሚያስችለውን አንቀጽ በሚመለከት ቢሮው መስማማቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣

ሸ/ በማንኛውም መስክ ለላቀ የሥራ ክንውን ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 134 መሠረት የሚሰጥ ሽልማት፣

ቀ/ በተቀባዩ ላይ በደረሰ ጉዳት ወይም በሌላ ሰው ሞት ምክንያት የሚከፈል ካሳ፣

በ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ስጦታው የመቀጠር፣ የኪራይ ወይም የንግድ ገቢ ካልሆነ በስተቀር በስጦታ ወይም በውርስ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም ንብረት፣

ተ/ በትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርትን በነጻ ለመከታተል የሚፈጸም ክፍያ

ቸ/ ለቀለብ ወይም ለህጻናት ድጋፍ የሚሰጡ ክፍያዎች፣

ኀ/ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ ህንጻ በማከራየት ወይም የንግድ ገቢን ሳይጨምር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚያገኘው ገቢ፣

ነ/ ገንዘብ በሚቆጠርበት ጊዜ ለሚደርሰው ጉድለት ማካካሻ በሚሆን መጠን ብቻ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው እና ለዚሁ ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የጥሬ ገንዘብ ማካካሻ ክፍያ፣

ኘ/ በኢትዮጵያ ጸንቶ በሚሰራበት ሕግ መሠረት በተለይ ከገቢ ግብር ነጻ የተደረገ ገቢ፣

አ). ለመኖሪያ ቤት ሠራተኞች የሚከፈል ደመወዝ፣

ከ) በነዳጅ ሥራ ላይ የተሰማራ ሥራ ተቋራጭ ለንዑስ ሥራ ተቋራጮች የሚፈጽመው ክፍያ።

(ሸ) በሰራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች አዲስ ከሚያወጡት አክሲዮን የሚገኝ የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም (ፕሪሚያም)፤

(ወ) ማናቸውም ኩባንያ በኩባንያው ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአስራ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ (12.5%) ያላነሰ ድምጽ የመስጠት መብት እና የኩባንያውን ውሳኔዎች የመቆጣጠር መብት ላለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚፈጽመው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍያ፤"

ፀ). የክለሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ለኢኮኖሚ፣ ለአስተዳደራዊ ወይም ለማህበራዊ ምክንያቶች አንድን ገቢ ከገቢ ግብር ነጻ ሊያደርግ ይችላል።

ክፍል ሰባት

የወል ደንቦች

ምዕራፍ አንድ

ሀብት

፷፮. ሀብት ስለማግኘት

አንድ ሰው ሀብት አገኘ የሚባለው ሕጋዊ የሀብት ባለቤትነት ስም ከተላለፈለት ጊዜ አንስቶ ሲሆን ሀብቱ መብት ወይም ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ ይህ መብት ወይም ምርጫ የተሰጠበትንም ጊዜ ይጨምራል።

፷፯. ሀብትን ስለማስተላለፍ

አንድ ሰው ሀብቱን አስተላለፈ የሚባለው ይህ ሰው ሀብቱን ሲሸጥ፣ ሲለውጥ ወይም በሌላ መንገድ በሀብቱ ላይ ያለውን የባለቤትነት ስም ሲያስተላልፍ ሲሆን፣ ሀብቱን እንዲሠረዝ፣

ለቀድሞ ባለቤቱ እንዲመለስ፣ እንዲጠፋ፣ እንዲወድም፣ ጊዜው እንዲያልፍ ወይም ለሌላ ተላልፎ እንዲሠጥ ማድረግን ይጨምራል።

፪) ማናቸውም ሰው ከዚህ ቀደም ያልነበረ ሀብቱ የሌላ ሰው ሀብት እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ፣ ይህንን ያደረገው ሰው ሀብቱ በተፈጠረበት ጊዜ በባለቤትነቱ ስም የነበረን ሀብት ለሁለተኛው ሰው እንዳስተላለፈ ይቆጠራል

፫). አንድ ሀብት በውርስ ወይም በኑዛዜ ከተላለፈ፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ሟቹ ሀብቱን እንዳስተላለፈ ይቆጠራል፡

፬). ሀብትን ማስተላለፍ የአንድን የንግድ ሀብት የተወሰነ ክፍል መሸጥ ወይም መለወጥንም ይጨምራል።

፭). ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአንድን ሰው ሀብት ("ባለቤቱ" ተብሎ የሚጠቀስ) ለአጣሪ፣ በኪሣራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ፣ ወይም ለተቀባይ መስጠት ሀብቱን እንደመሸጥ ወይም መለወጥ የማይቆጠር ሲሆን ከሀብቱ ጋር ተያይዞ በአጣሪው፣ በባለአደራው ወይም ባተቀባዩ የሚከናወኑ ተግባራት ባለቤቱ እንዳከናወናቸው ይቆጠራሉ፡

፷፰. ለሀብት የሚደረግ ወጪ

፩). የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሀብቶችን ሳይጨምር የአንድ ሀብት ወጪ የሚከተሉት ድምር ይሆናል፣

ሀ/ ሀብቱ በተገኘበት ጊዜ በዓይነት የሚሰጥን ሀብት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጨምሮ፣ ባለሀብቱ ለሀብቱ የከፈለው ዋጋ ሲሆን ሀብቱ የተገነባ፣ የተመረተ፣ ወይም የለማ እንደሆነ ለግንባታ፣ ለማምረት ወይም ለማልማት የወጣውን ወጪ ይጨምራል።

ለ/ ሀብቱ በማግኘት፣ በመሸጥ ወይም በመለወጥ ሂደት የወጣ ማንኛውም ወጪ፤

ሐ/ ሀብቱን ለመትከል፣ ለመቀየር፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት ወይም ለማሻሻል ባለሀብቱ ያወጣው ማንኛውም ወጪ፤

፪. ይህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሃብት ዋጋ ነው የሚባለው፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፯)(ሀ) (፩)፣(፪) ወይም (፫) "ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት" ስሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም

ከተመለከቱት ግዙፋዊ ሀልዎት ከሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ጋር በተያያዘ እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ለማሻሻል እና ለማደስ እንዲሁ እነዚህን ሀብቶች ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ የሚወጣ ሌላ ተጓዳኝ ወጪ፣

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፯)(ሀ) (፬) "ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት" ለሚለው ሀረግ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ ከተመለከተው ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት ጋር በተያያዘ የወጣ ወጪ ነው።

፫). በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ (፪) በተደነገጉት ሁኔታዎች መሠረት በስጦታ የሚገኝ ሀብት ወጪ ሀብቱ በስጦታ በተገኘበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው።

፬). የአንድ ሀበት ዋጋ በዚህ አዋጅ ተቀናሽ እንዲደረግ የተፈቀደውን ማንኛውንም ወጪ አይጨምርም።

፭). የአንድ ሀብት ዋጋ የሀብቱ ባለቤት ሀብቱን የማግኘት ምርጫ እንዲኖረው ከማድረግ ጋር በተያያዘ የወጡ ወጪዎችን ይጨምራል።

፮). የአንድ ሀብት ዋጋ በሀብቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በሀብቱ ባለቤት የሂሳብ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን ተቀናሽ ሂሳብ አያካትትም።

፯). አንድ ሰው ከአንድ ሀብት ውስጥ ከፊሉን የሸጠ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣ ይህ ሀብት ሲገዛ የነበረውን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ታሳቢ በማድረግ የሀብቱ ዋጋ በተሸጠው እና በባለሀብቱ እጅ ባለው ድርሻ መካከል ይከፋፈላል።

፰). በዚህ አዋጅ መሠረት በግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የተካተተ ካልሆነ በስተቀር፣ የአንድ ግብር ከፋይ ሀብት ዋጋ ግብር ከፋዩ ሀብቱን ሲያገኝ የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን ማንኛውንም ድጎማ፣ ተመላሽ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ማንኛውንም የገንዘብ ድጋፍ አይጨምርም።

፱). የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ የአንድን ሀብት ዋጋ ለመወሰን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባ ሌሎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን ሊወስን ይችላል።

፷፱. የንግድ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ የንግድ ሥራ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው ሀብቱን ለማግኘት ከወጣው ወጪ ላይ ከሀብቱ ጋር በተያያዘ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯(፩) መሠረት የተፈቀደው ተቀናሽ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯(፫)ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ የሚፈቀደው ተቀናሽ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ውጤት ነው።

፪). የአንድ ግብር ከፋይ የንግድ ሥራ ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ በሚሰላበት ጊዜ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ (፯) ተፈፃሚ የሚደረግ ከሆነ የንግድ ሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ነው የሚባለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ (፯)) መሠረት የሀብቱ ድርሻ ነው ተብሎ ከሚወሰደው ወጪ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯(፩) ለግብር ከፋዩ የሚደረገው የወጪ ተቀናሽ ወይም የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯(፬) ድንጋጌ ተግባራዊ ባይደረግ ኖሮ ተቀናሽ ይደረግ የነበረው ወጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሂሣብ ነው።

፶. ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ

፩). አንድ ሰው አንድን ሀብት ሲያስተላልፍ ከዚህ ሀብት የተገኘ ገቢ ሆኖ የሚወሰደው ሀብቱን ሲያስተላልፍ የተቀበለው ወይም የሚቀበለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ሲሆን፣ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ በዓይነት የተገኘውን ማንኛውንም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይጨምራል።

፪). ለኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማህበር የሚሰጥን እርዳታ ሳይጨምር ሀብት በስጦታ የተላለፈ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ያለው የሀብቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ከሀብቱ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

፫). አንድ ሰው ሀብቱን በማስተላለፍ ያገኘው ገቢ፣ ሀብቱን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ከቀረበለት ምርጫ ያገኘውን ጥቅም ይጨምራል። ሆኖም ይህ ጥቅም እንደገቢ ተደርጎ የሚወሰደው ከቀረበለት ምርጫ ጋር በተያያዘ ባገኘው ጥቅም ላይ ግብር ያልከፈለ ሲሆን ብቻ ነው።

፬). አንድ ሀብት የጠፋ ወይም የወደመ እንደሆነ፣ የዚህ ሀብት ዋጋ ነው የሚባለው ባለሀብቱ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ምክንያት የተቀበለው ወይም የሚቀበለው የካሳ መጠን ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

ሀ/ በመድን ፖሊሲ መሠረት፣ በካሳ ወይም በሌላ ስምምነት ምክንያት የተቀበለውን ወይም የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፣

ለ/ ቢድርድር ምክንያት የሚቀበለውን የገንዘብ መጠን፣ ወይም

ሐ/ የፍርድ ቤት ውሳኔን ተከትሎ የተቀበለውን ወይም የሚቀበሰውን የገንዘብ መጠን፣

፫). አንድ ሰው በአንድ ግብይት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀብቶችን ያስተላለፈ እንደሆነ የእያንዳንዱ ሀብት ዋጋ ተለይቶ ያልታወቀ እንደሆነ፣ ሀብቶቹ በተላለፈበት ጊዜ ባለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሠረት በማስተላለፉ ምክንያት የተገኘው የገንዘብ መጠን ሰተላለፉት ሀብቶች እንደየድርሻቸው ይደለደላል።

፬). አንድ ግብር ከፋይ የተላለፈውን ሀብት ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሀብቱ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

፶፩. ጥቅምን ወይም ኪሳራን ስለ ማስተላለፍ

፩). ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት አንድ ሀብት ሲተላለፍ የተገኘ ማናቸውም ዓይነት ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሳራ ለግብር አከፋፈል ከግምት ውስጥ አይገባም።

ሀ/ ባልና ሚስት በሚፋቱበት ጊዜ የሚደረግ የሀብት ክፍፍል፣

ለ/ አንድ ሰው በመሞቱ ምክንያት ለውርስ አጣሪው ወይም ለወራሹ ሀብት ሲተላለፍ፣

ሐ/ ሀብቱ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ ወይም ሀብቱ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በመንግሥት በመወሰዱ ምክንያት (ከዚህ በኋላ "የተተካው ሀብት" ተብሎ የሚጠቀስ) የተገኘው ገቢ ገንዘቡን በተቀበለው ሰው አማካኝነት ሀብቱ በጠፋ ወይም በወደመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ሀብት (ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት" ተብሎ የሚጠቀስ) ለማፍራት የዋለ እንደሆነ ወይም፣

መ/ ሀብቱ (ከዚህ በኋላ "የተተካው ሀብት" ተብሎ የሚጠራ) ዋጋው የሚቀንስ ሀብት የሆነ እንደሆነና ባለሀብቱ የተተካው ሀብት በጠፋ ወይም በወደመ በስድስት ወር ጊዜ ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ የረዘመ ጊዜ ውስጥ ሙሉ ባሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የሚውል ዋጋው የሚቀንስ (ከዚህ በኋላ "የመተኪያ ሀብት" ተብሎ የሚጠራ) ተመሳሳይ ሀብት ያፈራ እንደሆነ፣

፪). የተተካውን ሀብት ያገኘው ሰው ይህንን ሀብት ለወደፊት በሚያስተላልፍበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፍል የሚገባው ግብር የሌለ ሲሆን፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑም።

፫) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ወይም (ለ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ ሀብቱን ያገኘው ሰው ሀብቱን የሚያስተላልፈው ሰው ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ ለሀብቱ ባወጣው ወጪ የግንዘብ መጠን ልክ ሀብቱን እንዳገኘ ይቆጠራል።

፬). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) ወይም (መ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ከተተካው ሀብት ዋጋ የበለጠ እንደሆነ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከተተካው ሀብት ዋጋ ላይ ቢብለጫ የታየው የግንዘብ መጠን ተጨምሮበት ነው።

፭). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) ወይም (መ) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ ለተተካው ሀብት የተከፈለው ዋጋ ከመተኪያው ሀብት ዋጋ የሚበልጥ ከሆነ፣ የመተኪያው ሀብት ዋጋ ነው የሚባለው ሀብቱ ቢተላለፈበት ወቅት ያለው የተተካው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ቢብለጫ የታየው የግንዘብ መጠን ተቀንሶ ነው። ነገር ግን ከዜሮ በታች መሆን የለበትም።

፮). የሀብቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ለመቀነስ ያልዋለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ቢትርፍ የታየው የግንዘብ መጠን በግብር ክፋዩ ገቢ ውስጥ መካተት አለበት።

፯). የተላለፈው ሀብት ዋጋው የሚቀንስ ወይም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሀብት የሆነ እንደሆነ፦

ሀ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፫) "ለሀብት ባወጣው የግንዘብ መጠን" በሚል የተመለከተው አገላለጽ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

ለ/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) "ለተተካው ሀብት የተደረገ ወጪ" ስሚል የተመለከተው የተተካው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል።

፫፱. የተላለፉ ሀብቶችን ስለመመዝገብ

የአንድን ሀብት መተላለፍ ለመቀበል፣ ለመመዝገብ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ መተላለፉን ለማጽደቅ ብሀገ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሰው ቢሀብቱ መተላለፍ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሰረት መክፈል የሚገባው ማንኛውም ግብር መክፈሉን ሳያረጋግጥ መፈፀሙን ሊመዘግብ ወይም ሊያፀድቅ አይችልም።

ምዕራፍ ሁለት

ሌሎች የውል ድንጋጌዎች

፵፫. የተመለሰ ወጭ

አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ላወጣው ወጭ ተቀናሽ የተያዘለት እንደሆነ ወይም የማይሰበሰብ ዕዳ የተሰረዘለት እንደሆነ እና በቀጣይ ግን ግብር ከፋዩ በገንዘብ ወይም በዓይነት በተቀናሽ የተያዘለትን ወጪ ወይም የተሰረዘለትን ዕዳ የሚያካክስ የገንዘብ መጠን የተቀበለ እንደሆነ ግብር ከፋዩ የተቀበለው የገንዘብ መጠን ገንዘቡን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ገቢ የሚቆጠር ሲሆን ይህም ገቢ ተቀናሽ ተደርጐለት ከነበረው ገቢ ጋር ተመሳሳይ ምድብ ይኖረዋል።

፵፬. ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ስለማቆም

፩). ማናቸውም ግብር ከፋይ

ሀ. በግብር ዓመቱ ገቢው ከመገኘቱ በፊት ካቆመው የንግድ ሥራ፣ የሥራ እንቅስቃሴ፣ ወይም ኢንቨስትመንት ገቢ ያገኘ እንደሆነ፣

ለ/ ገቢው የተገኘው የንግዱ ሥራ፣ የሥራው እንቅስቃሴ ወይም ኢንቨስትመንቱ ከመቆሙ በፊት ቢሆን ኖሮ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት በሚሆንበት ጊዜ የንግዱ ሥራ፣ የሥራው እንቅስቃሴ ወይም ኢንቨስትመንቱ ገቢው በተገኘበት ጊዜ እንዳልቆመ ተቆጥሮ በገቢው ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ገቢ ለማግኘት የወጣ ወጪ በዚህ አዋጅ በሚፈቀደው መጠን በተቀናሽ ይያዛል።

፵፭. በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪(፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዓይነት የተገኘ የገንዘብ መጠን ወይም የተፈፀመ ክፍያ ዋጋ የገንዘቡ መጠን በተገኘበት ወይም ክፍያው በተፈፀመበት ጊዜ ሀብቱ የነበረው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ሲሆን፣ ይህ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ሀብቱን በማስተላለፍ መብት ላይ የተጣለው ገደብ ግምት ውስጥ አይገባም።

፰፮. ወጭዎችን ስለማከፋፈል

፩). የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማናቸውም ወጪ

ሀ/ ከአንድ በላይ የሆኑ የገቢ ዓይነቶችን ለማግኘት፣ ወይም

ለ/ አንድን የገቢ ዓይነት ለማግኘት እና ለሌሎች ዓላማዎች የዋለ እንደሆነ የሥራዎቹን ወይም የወጪዎቹን አንጻራዊ ባህርይና መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ወጪዎቹ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ይከፋፈላሉ።

፪). የሚከተሉት የተለያዩ የገቢ ዓይነቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

ሀ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤

ለ/ ቤትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

ሐ/ የንግድ ሥራ ገቢ፣

መ/ እያንዳንዱ ራሱን የቻለ የገቢ ዓይነት ሆኖ የሚወሰደው በሠንጠረዥ "መ" ሥር ግብር የሚከፈልበት ገቢ፣

ሠ/ ከገቢ ግብር ነፃ የሆነ ገቢ፤

፰፯. የገንዘብ ምንዛሪ

፩). በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰላ ግብር የገንዘብ መጠን በብር መገለጽ አለበት።

፪). የገንዘብ መጠን ከብር ወጪ በሆነ ገንዘብ የተያዘ ከሆነ፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የገንዘቡ መጠን በሂሳብ መዝገብ በሚመዘገብበት ጊዜ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው የምንዛሬ ተመን መሠረት ተሰልቶ ገንዘቡ ወደ ብር ይለወጣል።

፫). በውጭ ምንዛሪ በሚደረግ ግብይት የተገኘ ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሳራ ለግብር አከፋፈል ሲባል ግብይቱ በተከናወነበት የግብር ዓመት ውስጥ እንደተገኘ ጥቅም ወይም እንደ ደረሰ ኪሳራ ሆኖ መገለጽ አለበት።

ገቢዎች ቢሮ በውጭ ምንዛሪ ግብይት የደረሰ ኪሣራ ወይም የተገኘ ጥቅም የሚሰላበትን ዘዴ እና የውጭ ሀገር ገንዘብ ወደ ብር የሚቀየርበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፹፰. ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዘዴዎች

፩). ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ ቼክ፣ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ የባንክ ድራፍት፣ ከባንክ ሂሳብ ወደ ባንክ ሂሳብ ገንዘብ ቢማስተላለፍ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈጸሚያ መንገዶች ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ግብይቶች ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ መቀበል አይችልም።

ሀ) በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር በተደረገ ጠቅላላ ግብይት፣ ወይም

ለ) ከአንድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ክፍያ፣ ወይም

ሐ) ከአንድ ሰው ጋር ከተፈጸመ አንድ ግብይት ወይም ተግባር ጋር የተያያዘ ክፍያ፣

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፣

ሀ) በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ በባንኮች እና በማይክሮ ፋይናንስ ድርጅቶች፣

ለ) ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ወይም የተለዩ ግብይቶች፣

፫). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "**ግብይት**" ማለት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው የሚያከናውነው በዚህ አዋጅ መሰረት ግብር የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ነው።

፬) ገንዘብ ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በመመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

ክፍል ስምንት

ከግብር ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ስለመከላከል

፹፱. ገቢን መከፋፈል

፩). አንድ ግብር ከፋይ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በሚኖረው ግብይት ገቢን ለመከፋፈል ከሞከረ፣ ገቢው በመከፋፈሉ ምክንያት የሚደርሰውን የገቢ ግብር መቀነስ ለመከላከል ሲባል ባለሥልጣኑ የሁለቱን ሰዎች ገቢ እና ተቀናሽ ወጪ ሊያስተካክለው ይችላል።

፪). አንድ ግብር ከፋይ ገቢውን ለመከፋፈል ሞክሯል የሚባለው፦

ሀ/ ግብር ከፋዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ገቢውን ወይም ገቢውን የሚያስገኘውን ሙሉት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ፣

ለ/ ግብር ከፋዩ ጥሬ ገንዘብን ጨምሮ ማናቸውንም ንብረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍና ንብረቱ የተላለፈለት ሰው ከተላለፈው

ንብረት ገቢ ወይም ጥቅም ሲያገኝ፤ እንዲሁም ንብረቱ የተላለፈበት ምክንያት ወይም ከተላለፈባቸው ምክንያቶች አንዱ የአስተላላፊውን ወይም የተላለፈለትን ሰው ገቢ ዝቅ ለማድረግ ሲሆን ነው።

፫). አንድ ሰው ገቢውን ለመክፋፈል የሞከረ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ገቢዎች ቢሮ ለተላለፈው ንብረት የተሰጠውን ዋጋ (ካለ) ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

፴. ስለማሸጋገሪያ ዋጋ

፩). በገቢያ ዋጋ መርህ ያልተደረገ ማንኛውም ግብይት ሲኖር፤ በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚታየውን ትክክለኛ ገቢ፣ ጥቅም፣ ተቀናሽ፣ ኪሳራ፣ ወይም ማካካሻ ለመወሰን ገቢዎች ቢሮ እነዚህን ገቢዎች፣ ጥቅሞች፣ ተቀናሽ ወጪዎች፣ ኪሣራዎች ወይም ማካካሻዎች ግብይቱን ባደረጉት ወገኖች መካከል ሊያከፋፍል ወይም ሊደለድል ይችላል።

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈጻሚ በሚሆንበት ግብይት ከተዋዋዩቹ አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝና በኢትዮጵያ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆን እና የግብይቱ ሌላኛው ወገን ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ ማንኛውም ክፍፍል፣ ድለድል፣ የገቢ ክፍፍል፣ ጥቅም፣ ተቀናሽ ሂሣብ፣ ኪሣራ ወይም የግብር ማካካሻ የሚደረገው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት መካከል የገቢ ወይም የወጭ ድልድል የሚደረገው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚጣጣው መመሪያ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወኑ ግብይቶችም ተፈጻሚ ይሆናል።

፭). አንድ ግብር ከፋይ ለግብር ዓመቱ በሚያቀርበው የግብር ማስታወቂያ ውስጥ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር ያደረጋቸውን ግብይቶች ዝርዝር አብሮ ማቅረብ አለበት።

፮). በዚህ አንቀጽ "በገበያ ዋጋ መሠረት የሚደረግ ግብይት" ማለት ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች በገበያ ዋጋ መሠረት የሚያደርጉት ግብይት ነው።

፹፩. ከግብር ለመሸሽ የሚደረጉ ዕቅዶች

፩). የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፅመዋል ብሎ ሲያምን ገቢዎች ቢሮ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሀ/ ከግብር ለመሸሽ የሚያስችል ዕቅድ ሲዘጋጅ ወይም ተግባራዊ ሲሆን፣

ለ/ በዕቅዱ መሠረት አንድ ሰው የግብር ጥቅም ሲያገኝ፣

ሐ/ የዕቅዱን መሠረታዊ ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት በዕቅዱ የተሰማማው ወይም ዕቅዱን ተግባራዊ ያደረገው ሰው ይህንን ሊያደርግ የቻለበት ብቸኛው ወይም ዋነኛው ዓላማ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) የተመለከተውን የግብር ጥቅም ለማግኘት ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል ሲሆን ነው፡፡

፪). በዚህ አዋጅ ውስጥ ሌላ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም፣ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ሲሆን ባለሥልጣኑ ምንም ዓይነት የዕቅድ ስምምነት እንዳልተደረገ ወይም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳልተደረገ በመቁጠር ከግብር ለመሸሽ የተደረገውን ተግባር ለመከላከል ወይም ለመቀነስ አግባብነት ይኖረዋል የሚለውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበትን ሰው ወይም ከዕቅዱ ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው ግብር ሊወስን ይችላል፡፡

፫). በዚህ አንቀጽ መሠረት የግብር ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን፣ ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ ገቢዎች ቢሮ የግብር ውሳኔውን አስመልክቶ ለግብር ከፋዩ ማስታወቂያዎች ይሰጣል፡፡

፬) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም፡-

ሀ). "ዕቅድ"

ሀ/ በፍርድ ሂደት ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል ወይም የማይችል ቢሆንም፣ ወይም በግልጽ ወይም በአንድምታ የተደረገ ቢሆንም ባይሆንም፣ ስምምነትን፣ግመቻቸትን፣ ቃል ኪዳን መግባትን፣ ወይም አንድን ነገር ሥመፈፀም መስማማትን ይጨምራል፡፡

ለ/ ማንኛውንም ዕቅድ፣ ወይም ሀሳብ ማቅረብ፣ የአንድን ድርጊት ሂደት ወይም የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ይጨምራል፡፡

ለ) "የግብር ጥቅም" ማለት

፩/ ማንኛውም ሰው ሊከፍል የሚገባውን ግብር መቀነስ፣

፪/ የአንድን ሰው ግብር የመክፈል ኃላፊነት ማዘግየት፣ ወይም

፫/ ሌላ ማንኛውም ከግብር ሰመሸሽ የሚከናወን ድርጊት ነው።

ክፍል ዘጠኝ

አስተዳደራዊና የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች

፹፪. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚነት

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ይህንን አዋጅ ለማስተዳደር የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል።

፹፫. መዝገብ ስለመያዝ

፩). የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ መዝገቦችን የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ አለባቸው፡-

ሀ/ ቋሚ ሀብቶች የተገዙበትን ቀን፣ የተገዙበትን ዋጋ፣ ሀብቱን ለማሻሻል ይወጣውን ወጪ እና የሀብቱን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድን ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ መዝገብ፣

ለ/ ከግብር ከፋዩ ንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ማናቸውንም ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፣

ሐ/ ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የንግድ ዕቃዎችን ግዥና ሽያጭ እንዲሁም በግብር ከፋዩ የተሰጡ እና የተገኙ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን የሚያሳይ ሰነድ፣

፩. ለገበያ የቀሱትን ወይም የተቀበላቸውን የንግድ ዕቃዎች እና የተሰጠውን ወይም የተገኘውን አገልግሎት ዝርዝር፣

፪. ከግብር ከፋዩ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የገዙ ወይም ለግብር ከፋዩ ያቀረቡ ሰዎችን ስም እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (እንደሁኔታው)፣

፫. የአቅራቢውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞችን፣

መ/ በግብር ዓመቱ መጨረሻ በግብር ከፋዩ እጅ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ እና የዋጋ መገመቻ ዘዴን የሚያሳይ ሰነድ፣

ሠ/ የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ማንኛውም ሰነድ፣

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩(ሐ)(፫) ደረሰኝ የማይገኝላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ወጪው የሚያዝበትን ስርዓት ባለስልጣኑ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፬). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለማያቀርቡ ግብር ከፋዮች የንግድ ዕቃ ቆጠራ በአማካይ የቆጠራ ዘዴ ሆኖ ይወሰዳል።

፫) የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ። የያዙት የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከፍሉት ግብር የሚወሰነው በሂሳብ መዝገባቸው እና በዚህ አዋጅ ሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ይሆናል"

፬) በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም የደረጃ"ሀ" ወይም "ለ" ግብር ከፋይ የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታ አለበት፡-

ሀ/ ከኪራይ የሚገኘውን ገቢ የሚያሳይ ሰነድ፣

ለ/ ከቤቱ ጋር በተያያዘ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የተከፈሉትን ክፍያዎች የሚያሳይ ሰነድ፣

ሐ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰(፩)(ለ) ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ከቤቱ ጋር ተያይዞ የሚወጣውን ማንኛውንም ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፣

መ/ የሚከራየው ሕንጻ የተገኘበትን ቀን፣ ሕንጻው የተገኘበትን ዋጋ፣ ሕንጻውን ለማሻሻል የወጣውን ወጭ እና የህንጻውን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚሳይ ሰነድ፣

ሠ/ ቤቱን በሚመለከት የተደረገ ማንኛውንም የተከራይ አከራይ ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፣

፭). በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱፰ መሠረት ግብር የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ሀብት የተገኘበትን ቀን፣ የተገኘበትን ዋጋ እና ሀብቱን ለማሻሻል የወጣ ሌላ ማንኛውንም ወጪ፣ ሀብቱ በሚተላለፍበት ጊዜ የተገኘውን ገቢ የሚያሳይ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት።

፮). በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግብር ከፋዩ አንድ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ወይም በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተትለት የሚያስችለውን የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ገቢዎች ቢሮ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝ ወይም አንድ ወጪ በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ አይችልም።

፯). በሠንጠረዥ 'ሐ' መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እና ከአንድ በላይ በንግድ ሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፣ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለእያንዳንዱ የተለየ የሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ አለበት።

፰). ማናቸውም ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊይዝ የሚገባውን የሒሳብ መዝገብ ካላቀረበ ግብሩ በግምት ይወሰናል። ሆኖም ለደረጃ "ለ" በተቀመጠው የማስከፈያ ዘዴ መሰረት ሊስተናገድ አይችልም።

፱). ማናቸውም ሰው በሌላ ኩባንያ ውስጥ አክሲዮን ለመግዛት በተበደረው ገንዘብ ላይ የሚከፍለው ወለድ በወጪነት ይያዛል። ሆኖም የዚህ አይነቱ ወጪ ተቀናሽ የሚደረገው ድርጅቱ አክሲዮን ከገዛበት ድርጅት የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ የሚያገኝ ከሆነ ነው።ዝርዝሩ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፲). በቴክኒክ ሙያ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያወጡት ወጪ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፲፩). ገቢዎች ቢሮ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን ያወጣል።

፹፬. ግብርን ስለማሳወቅ

፩). አንድ ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከአንድ በላይ ለሆኑ ቀጣሪዎች የማይሰራ ወይም ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ካልሆነ በስተቀር ግብሩን የማስታወቅ ግዴታ የለበትም።

፪). አንድ ተቀጣሪ በአንድ አመት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ ቀጣሪ ያለው ከሆነ ወይም ከራሱ ገቢ ላይ ግብ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከሆነ፤ አመቱ በተጠናቀቀ በ፴ ቀን ጊዜ ውስጥ የተጠቃለለለውን ገቢውን ማስታወቅ አለበት።

፫). የተጠቃለለለውን ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ ለሌለበት ተቀጣሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፫ መሰረት ቀጣሪው በየአመቱ የሚሰጠው ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ ግብር መቀነሱን የሚያረጋግጠው ማስረጃ

ለዚህ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም ተቀጣሪው ለአመቱ ሊከፍል ለሚገባው ግብር በሚሰረዝነት የሚያገለግል ይሆናል።"

፬). የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የግብር ዓመቱን ግብር የሚያሳውቁት በሚከተሉት ጊዜያት ውስጥ ይሆናል፦

ሀ/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ፪አራት ወራት ጊዜ ውስጥ፤

ለ/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮ የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፤

፭). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የሚቀርብ የግብር ማስታወቂያ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ/ ለደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች፣ የግብር ከፋዩን የግብር ዓመቱን ትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የሃብትና እዳ መግለጫ፣ ወይም

ለ ለደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች፣ የግብር ከፋዩን የግብር ዓመቱን የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ እና የሃብትና እዳ መግለጫ፣

፮). ካገኘው ገቢ ላይ ግብሩ ተቀናሽ የተደረገ በመሆኑ ምክንያት ነፃ ካልተደረገ በስተቀር የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ያለው ግብር ከፋይ ገቢውን ያስገኘው ግብይት ከተደረገ ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ የግብር ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፹፩. አስተዳደራዊ መቀጫ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፰ የተደነገገውን በመተላለፍ በአንቀጹ ከተመለከተው መጣን ቢላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለ ግብር ከፋይ በትርፍ የተቀበለውን ገንዘብ እጥፍ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል።"

፹፪. ግብርን ስለመክፈል

፩). አንድ ተቀጣሪ ለወሩ መክፈል የሚኖርበት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የመክፈያ ጊዜ ግብር ከፋዩ የየሦስት ወሩን የግብር ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ጊዜ ነው።

፪). የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን

ሀ) ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር ሰኔ ፴ቀን በመጨ (ሃያ አምስተኛው ቀን) የሂሳብ ሪፖርት ኦዲያቀርቡበት ወር መጨረሻ ጀምሮ ቦሚቆጠር

በየሦስት የሶስት ወሩ በተጠናቀቀ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አስቀድመው ይከፍላሉ፤

ለ) የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርቱ መሰረት ሲከፍሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሦስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይሰጥላሉ፤

ሐ) የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት የግብር ስሌት ሲከናወን በየሶስት ወሩ የከፈሉት ሊከፍሉት ከሚገባው የበለጠ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የከፈሉት ሂሳብ ተመላሽ ይደረጋል። የተመላሹ ክፍያ የሚፈጸመው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት ለተመላሽ ተቀንሶ ከሚያዘው ሂሳብ ላይ ይሆናል።

መ) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለውን የቅድሚያ ግብር አፈጻጸም የሚወስን መመሪያ ገንዘብ ቢሮ ሊያወጣ ይችላል

፫). የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬(፯) የሚመለከተው ግብር ከፋይ ግብር መክፈያ ጊዜ ግብይቱን አስመልክቶ የግብር ማስታወቂያ መቅረብ የሚኖርበት ጊዜ ይሆናል።

፬) የደረሻ "ለ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚሰፍሉት ቦሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) ከቀደዝው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር 25% (ሃያ አምስት በሙቶ) ከሐምሌ ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚቆጠር በየሦስት ወሩ የሶስት ወሩ በተጠናቀቀ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አስቀድመው ይከፍላሉ፤

ለ) በየግብር ዓመቱ ሐምሌ ወር መጨረሻ ሊከፍሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሦስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይከፍላሉ፤"

፭). በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ ፪ እና ፬ የተደነገገው ቢኖርም ለመጀመሪያ ጊዜ የገባ ግብር የሚከፍሉ አዲስ ግብር ከፋዮች የመጀመሪያውን የግብር ዓመት በተመለከተ ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) የደረሻ "ሀ" አዲስ ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ ቢግብር ዓመቱ ሊከፍሉት የሚገባውን ግብር መክፈል አለባቸው።

ለ) የደረሻ "ለ" አዲስ ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሐምሌ ፴ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ግብሩን መክፈል አለባቸው።

፹፪. ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ በቅድሚያ ስለሚከፈል ግብር

፩). የሠንጠረዥ "ሐ" ግብር ከፋይ ለንግድ የሚሆኑ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ሲያስገባ የዕቃዎቹን የጉምሩክ ዋጋ፣ የመድን አረቦንና የማጓጓዣ ወጪ ፫% (ሦስት በመቶ) የንግድ ሥራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ይክፍላል።

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መክፈል የሚኖርበት ግብር የሚከፈለው ዕቃዎቹ በጉምሩክ ቁጥጥር ከመውጣታቸው በፊት ሆኖ፣ ይህም ግብር ከፋዩ ዕቃዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባቱ ተግባር በተከናወነበት የግብር ዓመት ከግብር ከፋዩ ላይ ከሚፈለገው ዓመታዊ የንግድ ሥራ ግብር እዳ ጋር ይካካሳል።

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሊካካስ የሚችለው በአንድ የግብር ዓመት በየጊዜው የተከፈለው የግብር መጠን ግብር ከፋዩ በዓመቱ መክፈል ከሚኖርበት የንግድ ሥራ የገቢ ግብር ዕዳ የበለጠ እንደሆነ፣ በልዩነት የታየው የገንዘብ መጠን በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፶ መሠረት ሥራ ላይ ይውላል።

፬). ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል "ለንግድ የሚሆኑ ዕቃዎች" የሚለው ሀረግ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ትርጉም የሚሰጠው ይሆናል።

ክፍል አሥር

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት

፹፫. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት

፩). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ቀጣሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት ከመቀጠር የሚገኝ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለተቀጣሪው በሚከፍልበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ በሚሆነው የግብር ምጣኔ መሠረት በእያንዳንዱ የክፍያ ጊዜ መክፈል የሚኖርበትን የገቢ ግብር ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

፪). ቀጣሪው ተቀጣሪው ከአንድ በላይ የሆነ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እንዳለው ያወቀና ሌላው ቀጣሪ ወይም ሌሎቹ ቀጣሪዎች በጠቅላላው የተቀጣሪው ገቢ ላይ ተመስረተው የገቢ ግብሩን ቀንሰው እንደማያስቀሩ ያወቀ እንደሆነ ቀጣሪው የተቀጣሪውን ገቢ በማጠቃለል የገቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

፫). ቀጣሪው ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታው ለሠራተኛው ከሚፈጽማቸው ክፍያዎች ላይ በቀጣሪው ተቀናሽ መደረግ ካለባቸው ሌሎች ግዴታዎች ቅድሚያ ይኖረዋል።

፹፱. በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆኑ ሰዎች ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት

፩). የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ያለው ቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ የንዑስ ሥራ ተቋራጭ ክፍያ፣ የወለድ፣ የሮያሊቲ፣ የሥራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒካል ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ወደ ወጭ የሚላክ ትርፍ ወይም የሌሎች ገቢዎች ክፍያ የፈፀመ እንደሆነ እንደአግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫(፬)፣ ፶(፫)፣ ፷፭፣ ፷፮ ወይም ፷፫ በተደነገገው የግብር መጣኔ መሠረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነው ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ቀንሶ መያዝ አለበት።

፪) የኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ያለው ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ አዝናኝ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ክፍያ የፈፀመ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫(፩) በተደነገገው የግብር መጣኔ መሠረት ለአዝናኙ ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ የገቢ ግብር ቀንሶ መያዝ አለበት።

፫) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ያልተከፋፈለ ትርፍ ያለው እንደሆነ ከዚህ ትርፍ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ ቢተደነገገው መሠረት ግብሩን ቀንሶ መያዝ አለበት።

፺. ከትርፍ ድርሻ፣ ካልተከፈለ ትርፍ፣ ከወለድ እና ከሮያሊቲ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ማስቀረት

፩). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው እና በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ መሠረት ግብር የሚከፈልበት የሮያሊቲ ክፍያ በሚፈፅምበት ጊዜ በዚያው አንቀጽ ቡተወሰነው ምጣኔ መሠረት ግብሩን ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ቀንሶ ማስቀረት አለበት።

፪). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት እንደአግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ወይም አንቀጽ ፶፯ መሠረት ግብር የሚከፈልበት የትርፍ ድርሻ ክፍያ ወይም ያልተከፈለ ትርፍ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ሲፈጽም ወይም ሲይዝ በዚያው አንቀጽ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

፫). በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ወለድ የከፈለ እንደሆነ በዚያው አንቀጽ ፬ተወሰነው የግብር ምጣኔ መሠረት ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

፶፩. በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት

፩). ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በስተቀር ማንኛውም ድርጅት፤ የመንግስት መስሪያ ቤት፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ ፫% (ሶስት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፦

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዢ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር ፳ (ሃያ ሺህ ብር) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት የሚፈጸም ክፍያ፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት አቅርቦት ውል ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በላይ የሚፈጸም ክፍያ፤"

፪) ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ገንዘብ በማያንስ መጠን ተነጣጥለው ሲቀርቡና እነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በመደበኛው አሰራር በአንድ አቅርቦት እንደሚቀርቡና ለአቅርቦቱ የሚከፈለው ገንዘብም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው የገንዘብ መጠን እንደሚበልጥ የሚገመት ከሆነ፤ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚ ይሆናል።

፫). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን የግብር መጠን በመወሰን እና የጹሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ያልተከፈለውን ተቀንሶ መያዝ የነበረበትን ግብር ከአቅራቢው ወይም ከገዥው ላይ ለማስከፈል ይችላል።

፬). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅራቢ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ክፋይ መለያ ቁጥሩን እና አግባብነት ያለው የታደሰ ንግድ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጡ ለማይገደዱ የሙያ ፈቃዱን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ ፴% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።"

፭). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ተይዞ የሚከፈለው ግብር፦

ሀ/ አቅራቢው ከአቅርቦቱ የሚያገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ግብር ይሆናል።

ለ/ በመመሪያ ወይም በአስተዳደራዊ ውሳኔ ቀሪ ሊደረግ አይችልም።

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ቢሮው በመመሪያ ሊለውጠው ይችላል።

፶፪. ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ስለመያዝ

፩). በማናቸውም ሕግ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የሌለበት ቀጣሪ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ከእነዙህ ተቋማት ከሚቀበለው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፱ በተደነገገው መሰረት ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ አለበት።

፪). የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀጠሪው ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፱ በተደነገገው መሰረት ግብሩን ቀንሶ በማይዝበት ጊዜ ብቻ ነው።

፫). ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በክልል ነዋሪ የሆነ እና ገቢውን ያገኘው ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ ፶፪ መሰረት ራሱ ግብሩን ቀንሶ ማስቀረት አለበት።

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ እና ፶፯ መሰረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ የሚከፍለው ሰው በክልሉ ውስጥ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የሌለውና የክልሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ሲሆን ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፭ መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ የሚከፍለው ሰው በኢትዮጵያ ወይም በክልሉ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን

፶፫. ከግብር ነፃ በሆኑ ገቢዎች ላይ ግብር ተቀንሶ የማይያዝ ስለመሆኑ

በዚህ ምዕራፍ መሠረት ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ከግብር ነፃ ባሆነ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ አይችልም።

፶፬ ግብር ተቀንሶ የሚያዝበት ገቢ ተከፈለ ስለሚባልበት ጊዜ

ለዚህ የአዋጁ ክፍል አፈጻጸም ሲባል፣ ግብር ተቀናሽ ናሚደረግበት ገቢ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ባለበት ሰው ተከፈለ የሚባለው ከሚከተሉት አንዱ ሲፈጸም ነው፡

ሀ/ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ክፍያ ለሚፈጸምለት ሰው በእርግጥ ሲከፈል፣

ለ/ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ በተከፋዩ ትእዛዝ ወይም በህግ መሠረት በተከፋዩ ስም ሲከፈል፣

ሐ/ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ለተከፋዩ ጥቅም ሲባል ሥራ ላይ ከዋለ፣ ከተጠራቀመ፣ ወይም ለካፒታል ንብረት ማሻሻ ሲውል፣

መ/ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ገቢ ለተከፋዩ ጥቅም ሲባል በተከፋዩ ስም ሲያዝለት

፶፩. ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ስለመስጠት

ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር ተቀንሶ በሚያዝበት ጊዜ፣ ግብሩን ቀንሶ የሚይዘው ሰው ክፍያውን ለሚቀበሉው ሰው ገቢዎች ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡

፶፪. ተቀንሶ የተያዘውን ግብር ስለመክፈል

፩). ማንኛውም ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚከፍሰው ገንዘብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ግብር ክፍያ ከፈፀመበት ወር በኋላ ባለው ወር ሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ፣ ለባለሥልጣኑ መክፈል ይኖርበታል፡፡

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀንሶ የሚያዝ ግብር የሚከፍል ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ተቀናሽ ተደርጎ የተያዘውን ግብር በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለባለሥልጣኑ የማስታወቅና ግብሩን አብሮ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

፫) ማንኛውም ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው፣

ሀ/ በዚህ የአዋጁ ክፍል በተደነገገው መሠረት ግብር ቀንሶ ያልያዘ ካሆነ፣ ወይም

ለ/ ቀንሶ የያዘውን ግብር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ለባለሥልጣኑ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ለባለሥልጣኑ መክፈል የሚኖርበትን ግብር በተመለከተ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፬). ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ግብሩን ቀንሶ ባለመያዙ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ለተመለከተው የግብር መጠን ኃላፊ በሚሆንበት ጊዜ እርሱ የከፈለውን ግብር ክፍያ ከተፈጸመለት ሰው ላይ የማስመለስ መብት አለው፡፡

፶፫. ተቀንሶ ለተያዘ ግብር የሚሰጥ የግብር ማካካሻ

፩). በዚህ ምዕራፍ መሠረት ከገቢ ላይ የተቀነሳው ግብር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፩) ወይም ፵፬(፪) መሠረት የመጨረሻ ግብር በማይሆንበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ተቀንሶ ለተያዘው ግብር የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተከፈለው ግብር ከግብር ከፋዩ ላይ በዓመቱ ከሚፈለገው የግብር መጠን ያነሰ እንደሆነ ግብር ከፋዩ ገቢውን በሚያስታውቅበት ጊዜ በልዩነት የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተከፈለው ግብር ከግብር ከፋዩ ላይ በግብር ዓመቱ ከሚፈለገው የግብር መጠን በልጦ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የተከፈለው ግብር በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፵፱ በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል አሥራ አንድ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶፮. ደንብና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

፩). ለዚህ አዋጅ ትክክለኛ አፈጻጸም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤቱ ደንብ ያወጣል።

፪). ቢሮው ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለሚወጣው ደንብ ትክክለኛ አፈጻፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፫). በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ በዚህ አዋጅ ተለይቶ በተሰጠው ጉዳይ ላይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፶፯ የገቢ ግብር ማበረታቻ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈፃፀም

፩). በኢንቨስትመንት ሕጉ መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንቬስተሮች ሊሰጣቸው የሚገባው የገቢ ግብር ማበረታቻ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሰረት መሆን አለበት።

፪). በዚህ አዋጅና አዋጁን መሰረት በማድረግ በሚወጣው ደንብ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ከተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች ውጭ የተሰጡ ማናቸውም ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

፫). በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም፣ በጎበረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ በተደነገገው መሰረት ማኅበሩ በሚያገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ የገቢ ግብር ተፈጻሚ አይሆንበትም።

፱. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩). የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸/፪ሺ፰ እና የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፫፺/፪ሺ፲፫

፪). የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር ፹፫/ ሺ ፱፻፺፩፣የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/ ፪ ሺ፫፣ ፪፻፲፪/፪ ሺ፯ እና ፱፻፫ ፯/፪ሺ፲፫

፫). በዚህ አዋጅ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች የተሻሻለው የማዕድን ሥራ ፈቃድ ፣ የማእድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የማእድን ኪራይ ክፍያዎች መወሰኛ ደንብ ቁጥር ፪፻፭/፪ ሺህ ፲፬

፬). ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

፲፭. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩). ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከሚሆንበት የግብር አመት በፊት ላለው የግብር አመት ያልተሰበሰበ ግብርን በተመለከተ ከመሻሻሉ በፊት የነበረው የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች እና የተሻረው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

፪). በተሻሩት ሕጎች መሠረት የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

፲፮. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ ይህ አዋጅ ከሚከተለው ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፦

፩). በዚህ አዋጅ የተጣለው አማራጭ አነስተኛ ግብር ከሃምሌ ፩ ቀን ፪ ሺህ ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ በሚሰበሰብ ግብር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

፪). በሰነጠረዥ "መ" መሰረት የሚሰበሰብ ግብር እና በአንቀጽ ፶፪ መሰረት ከግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው ግብር ከነሃሴ ፩ ቀን ፪ ሺህ ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፤

፫) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የዚህ የማሻሻያ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ከሃምሌ ፩ ቀን ፪ ሺህ ፲፯ ዓ.ም ዓ.ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ይሆናል።

ባህር ዳር ታህሳስ 17 ቀን ፪ ሺህ ፲፮ ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት